# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 306 ሐምሌ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# «አገልግሎትን በገንዘብ በመሸጥና በሌብነት ሕዝቡን እያማረሩ ያሉ አካላትን መንግሥት አይታገስም»

- ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ሚኒስትር

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አገር የማፍረስ ተልዕኮ አንግበው በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች አገልግሎትን በንዘብ በመሸጥና በሌብነት ሕዝቡን እያማረሩና አገሪቱን እየጎዱ ያሉ አካላትን መንግሥት እንደማይታገስ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ሚኒስትር ዶክተር ቢቂላ ሁሪሳ ገለጹ።

ዶክተር ቢቂላ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደገለጹት፣ በየመሥሪያ ቤት በሥራ ቅጥር፣ በደረጃ እድገት ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት ገንዘብ የሚጠይቁና ሌብነት ላይ የተሰማሩ አካላት ተልዕኮአቸው ለውጡን ለመቀልበስ ብሎም በህዝብና በመንግሥት መካከል መተማመን እንዳይኖር በማድረግ አገር ለማፍረስ ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አንዱና ዋነኞቹ በመሆናቸው መንግሥት ጠንካራ እርምጃ የሚወስድ ይሆናል።

ህዝቡም የገፈቱ ቀማሽ እንደ መሆኑ መጠን ተጨባጭ መረጃዎችን ለመንግሥት አካላት በማቅረብና አገልግሎት በነጻ የማግኘት መብቱን በማስከበር ሌቦችን በማጋለጥ የዜግነት ግዴታውን መወጣት ይጠበቅበታል ሲሉም ተናግረዋል።

የሥራ አጥነትን ችግር እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ዛሬም አንዳንድ መሥሪያ ቤቶች ጽዳት ሰራተኛ እንኳ ለመቅጠር ገንዘብ የሚጠይቁ አካላት እንዳሉ የጠቆሙት ዶክተር ቢቂላ፣ እንዲህ አይነት ሌቦችን በጋራ መከላከል እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ዶክተር ቢቂላ እንደገለጹት፤ በመስጠት ከተቀጠሩ

«አገልግሎትን በገንዘብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ከፋይል







# «ለሶስተኛ ወገን ፍላጎት በቆሙ የሱዳን መሪዎች በኢትዮጵያ ላይ በየዘመኑ ደባዎች ሲፈጸሙ ኖረዋል»

- ፕሮፌሰር አደም ካሚል

የታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፦ የሶስተኛ ወገን ፍላጎትን ለማስፈጸም በቆሙ የሱዳን መሪዎች በኢትዮጵያ ላይ በየዘመኑ ደባዎች ሲፈጸሙ እንደኖሩ የታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊው ፕሮፌሰር አደም ካሚል ተናገሩ።

ፕሮፌሰር አደም ካሚል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የሱዳን እና የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት የቆየ ወዳጅነትና ወንድማማችነት ያለው ህዝብ ነው።

ሁለቱ ህዝቦች በታሪካቸው፤ በባህላዊ እሴቶቻቸው እና አኗኗራቸው የጋራ እሴቶች ያዳበሩና ተቀራራቢ ስነልቦና ያላቸው ህዝቦች ናቸው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፣ ነገር ግን ለግብጽ ተላላኪ የሆኑ የሱዳን መሪዎች የሁለቱን ሃገራት ህዝቦች ለመለያየት ለበርካታ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ትንኮሳ በማድረግ ህዝቦቹን ለመለያየት ሙከራ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ጠቁመዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም እንደገለጹት፤ በየዘመናቱ

«ለሶስተኛ ወገን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ከፋይል

# የባለሙያዎች የማስፈጸም አቅምና የግብር ከፋዮች ግንዛቤ ማደግ የግብር አሰባሰቡን ውጤታማ እንዳደረገው ቢሮው አስታወቀ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የባለሙያዎች የማስፈጸም አቅማና የግብር ከፋዮች የግንዛቤ ማደግ የግብር አሰባሰቡ ውጤታማ እንዲሆን ማድረጉን የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ። የግብር አሰባሰብ ሥራው ውጤታማ እንዲሆን ኢቲ ታክስና ቴሌ ብር ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸውን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ በቢሮው ለመሰብሰብ የታቀደው ገቢ 48ነጥብ5 ቢሊዮን ብር ቢሆንም እስካሁን ባለው መረጃ 55 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል። በዚህም የእቅዱን ከ114 በመቶ በላይ ማሳካት ተችሏል።

ውጤቱ እንዲመዘገብ ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥም አሰራሮችን የማዘመን ሥራ መሰራቱ፤ የአመራሩን አቅም በማሳደግ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ጠንካራ አመራሮች ሥራውን እንዲሰሩ ስምሪት መደረጉ፣ በልዩ ልዩ ስልጠናዎች የባለሙያዎችን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ መቻሉ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

በየጊዜው የሚወጡ አሰራሮችንና

የባለሙያዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አቶ ሙሉጌታ ተፈራ



ዜና




በቢሾፍቱ ከተማ የተካሄደው የምክክር መድረክ

# የዴሞክራሲ ተቋማትን አቅም ለማጠናከር የሕግ ማሻሻያዎች ይደረጋሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የዴሞክራሲ ተቋማትን አቅም ለማጠናከር የሕግ ማሻሻያዎች እንዲደረጉና መንግሥታዊ ድጋፎች እንዲጠናከሩ እንሰራለን ሲሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ገለጹ።

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ የዴሞክራሲ ተቋማት ያከናወኗቸውን የማሻሻያ የለውጥ ሥራዎች የተመለከተ የምክክር መድረክ ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤የተቋማት መጠናከር በአንድ አገር ውስጥ ሥርዓት እንዲኖርና አገርም እንዲገነባ ዋነኛ መሰረት መሆኑን አመልክተው፤ የተቋማቱን አቅም የሚያጎለብቱ የሕግ ማሻሻያዎችና መንግሥታዊ ድጋፎች እንዲጠናከሩ እንሰራለን።

የዴሞክራሲ ተቋማትን "የምክር ቤቱ ክንዶች" ናቸው ሲሉ የገለጹት አፈጉባኤ ታገሰ፤ በተቋማት ግንባታ ሂደት ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጀምሮ የዴሞክራሲ ተቋማት ፅኑ መሰረት ሊኖራቸው ይገባልም ብለዋል።

የሕግ ማዕቀፎችን የማሻሻል፣ ወቅቱን ያማከሉ የቴክኖሎጂ ለውጦችና የሰው ኃይል ክህሎትን የማሳደግና አቅም የማደራጀት ተግባራት መከናወናቸውንም አብራርተዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ክርስትያን ታደለ፤ በበኩላቸው በሚዲያ ተቋማት "የተለያዩ ድምፆችን የማስማትና የፍትሐዊነት ችግሮች ስለሚስተዋሉ ሊስተካከሉ ይገባል" ብለዋል።

የዴሞክራሲ ተቋማቱ ሪፖርት በማውጣት ብቻ ገለልተኝነታቸውን ከማሳወቅ አልፈው ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታት የቁጥጥር ሥራ እንዲከናወን መስራት አለባቸው ብለዋል።

በመድረኩ የተቋማት ኃላፊዎች የሚዲያ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተው መልካም ተሞክሮዎችን በማስቀጠል ችግሮችን መፍታት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መክረዋል። በመድረኩ ላይ የተወሰኑ ተቋማት ያከናወኗቸው የማሻሻያ ሥራዎችና ያጋጠሟቸው ችግሮች ቀርበው ውይይት እንደተደረገባቸው የኢዜአ ዘገባ ያመለክታል።

# የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች መንግሥት ባወጣው ታሪፍ ብቻ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች መንግሥት ባወጣው ታሪፍ ብቻ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ተገለጸ።

የአማራ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ፣ የአማራ ክልል ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ባለስልጣን እንዲሁም ኢትዮ ቴሌኮም ሰሜን ምዕራብ ሪጂን በጋራ በመሆን በሀገሪቱ እየተተገበረ ያለውን የነዳጅ ድጎማ አስመልክተው መግለጫ ሰጥተዋል።

የአማራ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ የንግድ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ፈንታው ፈጠነ፣ የነዳጅ ድጎማው ዋና አላማ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የነዳጅ ግብይት ችግር ለመፍታት ነው ያሉ ሲሆን በዓለም ገበያ ያለው የነዳጅ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ የነዳጅ ዋጋ መሸጫ ማስተካከያ በማድረግ እና የድጎማ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎችን በመለየት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የማድረግ አሰራር ተጀምሯል ብለዋል።

በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እና ድጎማ ወደ አገር የሚገባውን ነዳጅ ለታለመለት አላማ እንዲውል ሪፎርም ተሰርቶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣ በክልሉ አገልግሎት ከሚሰጡ 225 የነዳጅ ማደያዎች መካከል 213 ማደያዎች በቴሌ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ተመዝግበው ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ተናግረዋል።

በቀጣይም ሁሉም ማደያዎች በቴሌ ብር ግብይት እንዲፈጽሙ አሰራር ተዘርግቷል። ይህም ጊዜን፣ ወጪን እንዲሁም ግብይትን በየትኛውም ቦታ ሆነው ለመፈጸም ያስችላል ብለዋል።



የአማራ ክልል ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ባለስልጣን የትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ስምሪት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደመላሽ ሽንሻው በበኩላቸው የነዳጅ ድጎማው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍል ያለመ በመሆኑ ለህዝብ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ለድጎማው ተመርጠዋል።

በዚህም መሰረት የህዝብ ትራንስፖርትና የከተማ ትራንስፖርት ተለይተው የድጎማው ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለዋል። ድጎማው የማይመለከታቸው ተሽከርካሪዎች ደግሞ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች፣ የግል አውቶሞቢሎች፣ ኮንትራት የገቡ የህዝብና የከተማ ትራንስፖርቶች፣ የጭነት ትራንስፖርቶች እና የኤርፖርት ታከሲዎች ናቸው።

አቶ ደመላሽ አክለውም በክልሉ 41ሺህ 279 የከተማ ትራንስፖርትና 8ሺህ 813 የህዝብ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ተመዝግበው ለፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ ባለስልጣን መተላለፋቸውን ገልጸው የድጎማው ተጠቃሚ የሆኑ ተሽከርካሪዎች መንግሥት ባወጣው ታሪፍ መሰረት የማገልገል ግዴታ እንጂ እንደፈለጋቸው ኮንትራት መስራት አይፈቀድላቸውም ሲሉ አሳስበዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የነዳጅ ድጎማውን እውን ለማድረግ ከአንድ ወር በፊት የተሽከርካሪዎችን ባለቤት፣ ሰሌዳ ቁጥር፣ የአሽከርካሪውን ስምና ስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የነዳጅ ወኪሎችን በመመዝገብ ሥራ ጀምሯል።

በሂደቱም የአሽከርካሪዎች አጠቃቀም ግንዛቤ ማነስ፣ የይለፍና የፒን ቁጥር መዘንጋት ያጋጠሙ ችግሮች ሲሆኑ፣ ደንበኞች ቁጥራቸውን ሲዘነጉ ወደ 127 በመደወል ማስተካከል እንደሚችሉ የኢትዮ ቴሌኮም ሰሜን ምዕራብ ሪጂን ኦፕሬሽን ዳይሬክተር አቶ አበበ ጥሩነህ መናገራቸውን ከክልሉ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ዜና

# በገቢ፣ በኤክስፖርትና ፋይናንሻል ዘርፎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መመዝገባቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በገቢ ፣ በኤክስፖርት፣ በውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትና በፋይናንሻል ዘርፎች እንደአገር ተስፋ ሰጪ ውጤት መታየቱን የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 16ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ ተገኝተው የኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ለምክር ቤቱ በሰጡት ማብራሪያ፤ በተለያዩ ዘርፎች የተገኘው ውጤት በቀጣይ ጊዜያትም እንደሚጨምር የማክሮ ኢኮኖሚ አቅጣጫው ያሳያል። በእያንዳንዱ ዘርፍ የታየውን ውጤትም አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ መንግሥት በ2014 በጀት ዓመት 330 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ እንደነበር ጠቁመው፤ በ11 ወራት ብቻ 309 ቢሊዮን ብር ሰብስቧል። ይህም የዕቅዱ 93 በመቶ እንደሆነ ጠቁመዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ገቢው ዓምና በተመሳሳይ ወር ከተሰበሰበው አንጻር የ50 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አለው። ይሄን ያመጣው በገቢ መስሪያ ቤቱ ላይ ያሉ አመራርና ሰራተኞች በጥረት በመስራታቸው ነውና ምስጋና ይገባቸዋል።

ከዚህ ባለፈ ነጋዴዎችም አገራዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ያላቸው ፍላጎት ማደጉ ገቢው እንዲጨምር አንድ ምክንያት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይሁንና አሁንም ኢትዮጵያ መሰብሰብ ከሚገባት ገቢ አንጻር ዝቅተኛውን እየሰበሰበች መሆኑን ማሰብ ይገባል ብለዋል።

ምክንያቱም የመንግሥት ወጪውን ብናይ በ11 ወር 500 ቢሊዮን ብር ሆኗል፤ ይህም በገቢ እና ወጪ በኩል አለመመጣጠን እንደሚያሳይ ጠቁመዋል።

ወጪን ያበዛው ዋናው ጉዳይ ያለብን እዳ እንደሆነም ጠቁመው፤ ልክ ልማቱ ላይ ርብርብ እንደምናደርገው ዕዳችንን እየከፈልን ከስጋት ቀጠና ነፃ ለመውጣት ቁርጠኝነት አለን ብለዋል። በዚህ ዓመት ብቻ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዶላር ዕዳ መከፈሉንም ጠቅሰዋል።

ሌላው ከፍተኛ ውጤት የተገኘው በኤክስፖርት እንደሆነ የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለዚህም ውጤት በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ሴክተር ተሳታፊ የነበሩ ተዋናዮች ምስጋና እንደሚገባቸው አስታውቀዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሆነ፤ በኤክስፖርት የተገኘው እመርታ ግዙፍ ነው፤ ከ10 ዓመት በፊት ኤክስፖርት ገቢ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነበር። በሁለት ዓመት ውስጥ በተሰራው ሪፎርም በሸቀጥና አገልግሎት ዘርፎች 10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥ የ25 በመቶ ዕድገት ያስገኘው የአገልግሎት ዘርፉ ከስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ አስገኝቷል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ይህ ውጤት የለውጡን ስኬት የሚያሳይ ነው። ይህን አስጠብቀን ከቀጠልን የወጪና ገቢ ንግድ መዛባቱን አስተካክለን የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን መቅረፍ ያስችለናል ብለዋል።

የወጪ ንግዱ ገቢ የተገኘው አንድ በግብርና ሥራችን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ቡና በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ11 ወር ከአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ኤክስፖርት አድርገናል፤ በየዓመቱ የምንተክላቸው የቡና ችግኞች ውጤት እያመጡ ነው። ይህን በቡናና ሻይ እንዲሁም በአትክልት ምርትም እንደግመዋለን ሲሉ ተናግረዋል። በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፉ ኤክስፖርት ለማሳደግ ከአምና የተሻለ የቱሪዝም መዳረሻ እያሰፋን በመሆኑ አገልግሎቱም የበለጠ ገቢ እንደሚያስገኝ ይጠበቃል ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ በቀጣይ የአገሪቷ ሰላም እየተረጋገጠ ሲሄድ ደግሞ የቱሪዝም ገቢው የበለጠ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ዐቢይ ከሆነ፤ በተመሳሳይ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ዘንድሮ ካለፈው ዓመት የ10 በመቶ ዕድገት ተገኝቶ ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ሀብት መጥቷል።

በርካቶች ኢትዮጵያ ችግር ላይ ነች ይላሉ፤ እኛም ብዙ ድጋፍ ባልሰጠንበት ሁኔታም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እያደገ ነው። ስለዚህ ከገባንና ከሰራን አገራችን ላይ ተስፋ አለ ብለዋል።

በፋይናንሻል ሴክተሩም በተወሰደ ማስተካከያ መሰረት ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን የገለጹት ዶክተር ዐቢይ፤ የባንኮች አጠቃላይ ሀብት ሁለት ነጥብ ሶስት ትሪሊዮን ብር መድረሱንና ሃብታቸው የ21 በመቶ ዕድገት እንዳለው አስታውቀዋል።

ባንኮች 8ሺ242 ቅርንጫፍ አላቸው፤ ተደራሽነታቸው እየሰፋ ነው፤ የባንክ ደንበኞች ቁጥር 82 ነጥብ አራት ሚሊዮን ደርሷል ሲሉ አስረድተዋል።

ከባንክ ደንበኞች አንድ ነጥብ ስድስት ትሪሊዮን ብር ተቆጥቧል። ዘንድሮ ለብድር የዋለው ገንዘብ 353 ቢሊዮን ብር ነው። ከዚህ ውስጥ ዋናውን የብድር ድርሻ የሚወስደው የግል ሴክተሩ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ በአጠቃላይ በመንግሥት ሪፎርም አማካኝነት በተለያዩ ዘርፎች የታየውን ተስፋ ሰጪ ውጤት ይበልጥ ለማጠናከር ሁሉም አካል የበኩሉን ሚና ሊወጣ ይገባል።



## ኮሚሽኑን የትምህርት ማዕከል ለማድረግ የተያዘው እቅድ ተግባራዊ እየሆነ መሆኑ ተገለጸ

ዘላለም ግዛው

ባቱ፡- የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የትምህርት ማእከል እንዲሆን በመንግሥት የተቀመጠውን አቅጣጫ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ሊበረታታ እንደሚገባው የፍትህ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌድዮን ጢሞቴዎስ ገለጹ።

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራና የበጎ አድራጎት ማስጀመሪያ መርሐ ግብርን በባቱ ከተማ ያስጀመሩት ዶክተር ጌድዮን፤ ኮሚሽኑ የትምህርት ማዕከል እንዲሆን በመንግሥት የተቀመጠውን አቅጣጫ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ ሊበረታታ ይገባዋል ብለዋል።

በዝዋይ ማረሚያ ማእከል የተመለከቷቸው የእርሻ ልማት ሥራዎች እና የግንባታ እንቅስቃሴዎች ጥሩ ደረጃ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ዶክተር ጌዲዮን፤ ጅማሮውን ማስፋትና ማጠናከር ይገባል፣ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ ተምሳሌት መሆን አለበት ብለዋል።

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽነር ጀነራል ዳመነ ዳሮታ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ሥራው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ነው፣ የእርም ሥራዎችን በመስራት ታራሚዎች የእርም ጊዜያቸውን ጨርሰው ከማሕበረሰቡ ጋር በሚቀላቀሉበት ጊዜ ቴክኖሎጂና ግብዓቱን በመጠቀም በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በመቀናጀት በዘርፉ በመሰማራት ምርታማ ለመሆን የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲጨብጡ ይደረጋል።

የአካባቢው ስነ ምህዳር ለአቮካዶ ምርት ምቹ እንደመሆኑ ለአቮካዶ ምርት የበለጠ ትኩረት እንደተሰጠው የተናገሩት ኮሚሽነር ጄኔራሉ፤ ዙሪያው ደንና የፍራፍሬ ምርትም ምሳሌ የሆነበት አካባቢ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ኮሚሽነር ጄኔራል ዳመነ፣ አራት አይነት የአቮካዶ ምርት ዝርያ ችግኞች እንደተዘጋጁም አመልክተዋል። አምስት ሺህ አቮካዶ፣ አምስት ሺህ ፓፓያ፣ የእንስሳት መኖና የማስዋቢያ የዛፍ ችግኞች ይተከላሉ፣ በሁሉም ማዕከላት በክረምት ወቅት በድምሩ 72 ሺህ የደን ተከላ ታቅዷል። 40 ሺህ የሚሆኑት ችግኞች የሚተከሉት በዝዋይ ማዕከል ነው ብለዋል።

ትግበራው የአየር ንብረት እና የአፈር መሸርሸርን ከመከላከል ባሻገር በተለይም በፍራፍሬ ዘርፍ አካባቢው የማስተማሪያ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ የሚያስችል ትግበራ መሆኑን የጠቆሙት ኮሚሽነር ጄኔራል ዳመነ፣ በፍራፍሬ በተለይም በአቮካዶ ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችለውን ልማት ለማከናወን እንደሚረዳ ተናግረዋል።

የባቱ ከተማ አስተዳደር ተወካይ አቶ ሮባ ኢሬሶ በበኩላቸው፤ ትግበራው ለማረሚያ ቤቱ ብቻ ሳይሆን ለከተማ አስተዳደሩም ግብአት የሚሆን ነው። የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት መርሐ ግብርም ሆነ በአረንጓዴ አሻራ ትግበራው የከተማ አስተዳደሩን በመደገፍ አሳክታችኋልና ምስጋና ይገባችኋል ብለዋል።

የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የልማት ሥራና ማቋቋም ዳይሬክተር አቶ ዘሪሁን ኃይለማርያም፤ ቀደም ሲል የማንጎ ችግኝ ተተክሎ የነበረ ቢሆንም የአፈሩ ባሕሪ ሊስማማቸው ባለመቻሉ ለመቀየር መወሰኑን ተናግረዋል። የተተከሉት የአቮካዶ ችግኝ ዝርያዎች ለአካባቢው ስነ ምህዳር ምቹ መሆናቸውንም ተናግረዋል። 14 ሄክታር የሚሆነው አቮካዶና ፓፓያ ችግኞች በሕግ ታራሚዎች እንደሚተከልም ጠቁመዋል።

በፍትህ ሚኒስትር አስተባባሪነት ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን ኢትዮጵያን አረንጓዴ እናልብስ አራተኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በዝዋይ ማረሚያ ማዕከል ይፋ የሆነው የክረምት መርሐ ግብር፤ የደን ተከላ፣ የእርሻ ሥራዎች ጉብኝት እና በከተማው የአቅመ ደካሞች የቤት እድሳት ማስጀመር ተከናውኗል።

# «በየአቅጣጫው የተከፈተብንን ጥቃት ማክሸፍ የምንችለው መደማመጥና መተባበር ስንችል ብቻ ነው“

- ዶክተር ይልቃል ከፋለ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- በአማራ ሕዝብ ላይ እየተፈጸሙ ያሉ ጥቃቶች ማክሸፍ የሚቻለው በመደማመጥና በመተባበር ብቻ መሆኑን የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለጹ።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ከሰሜን ሸዋ ዞን የኅብረተሰብ ተወካዮች ጋር በደብረ ብርሃን ከተማ ሲወያዩ እንደገለጹት፤የአማራ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በሸኔ እና ትህነግ ኃይሎች መጠነ ሰፊ ጥቃቶች እየፈፀሙበት ነው ። እነዚህን ጥቃቶች ማክሸፍ የሚቻለው ደግሞ በመደማመጥና በመተባበር ብቻ ነው።

ይህን መጠነ ሰፊ ጥቃትና ጥፋት የሚያቀነባብሩት በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጭ ያሉ ሃይሎች እያደረሱት ያለውን የጥፋት አጀንዳ ለማክሸፍ ጠንካራ መንግሥታዊ መዋቅር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ የክልሉ መንግሥት ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እየሠራ ነው ብለዋል።

በክልሉ ውስጥ ለአብነት ከሰሞኑ በአጣዬና አካባቢው የደረሰው ጥቃት በተደጋጋሚ ጥፋት በመፈጸም መንግሥትን እረፍት ለመንሳት የሸብር ቡድኖች የጠነሰሱልን ሴራ አካል ነው ብለዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች በሚደርሱ ጥፋቶች ሁሉ የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ ኀዘን እንደሚሰማው የገለፁት ርዕሰ መስተዳድሩ የዚህ ሁሉ ችግር ማሰሪያው ሰከን ባለ መንገድ ስር የሰደዱ ችግሮችን ለመፍታት ተደማምጦ በመሥራት በመሆኑ ለዚህ ተግባራዊነት ሁሉም ሊረባረብ ይገባል ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት ከውስጥም ከውጭም እየደረሱ ያሉ ጫናዎችን ለመቋቋም በሰከነ መንገድ ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ርዕሰ መስተዳድሩ ተናግረዋል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየደረሱ ያሉ ጥቃቶችን ለማስቆም ከክልሎች ጋር እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

“ጠላቶቻችን ፍላጎታቸው በሚቀዱልን ቦይ ብቻ እንድንሄድ ነው፤ እኛ ግን ከዚህ አዙሪት ወጥተን የሕዝቡን ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ እንሠራለን፤ እየሠራንም ነው” ብለዋል።

ተፈናቃይ ወገኖችን ከጊዜያዊ መጠለያ በዘለለ በዘላቂነት መብታቸው ተከብሮ የሚኖሩበትን ምህዳር ለመፍጠር ጠንካራ ሥራ ይጠበቅብናል ሲሉም ገልጸዋል።

ዶክተር ይልቃል ለዚህ ሁሉ ምስቅልቅል ምክንያት የሽብር ቡድኖቹ ሸኔና የትህነግ ሴራ መሆኑን የጋራ አቋም ልንይዝ ይገባናል ነው ያሉት።

በአማራ ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት የመጀመሪያ ተጎጅ አማራውን ያድርግ እንጂ የመላው ኢትዮጵያውያን ጥቃት መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ እየደረሰ ያለውን ጥፋት በቃ ሊለው እንደሚገባ አሚኮ ዘግቧል።



# የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችና ተፋሰሶች በመጤ አረም እየተጠቁ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችና የተፋሰስ ሃብቶች በመጤ አረም እየተጠቁ በመሆኑ ተገቢው እንክብካቤ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተገለጸ።

በኢፌዴሪ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተቀናጀ ውሃ ሀብት አስተዳደርና የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጉዳዮች አማካሪ አቶ አስማማው ቁሜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ የሚገኙት የስምጥ ሸለቆ የተፈጥሮ ሐይቆችና የተፋሰስ ሀብቶች በመጤ አረሞች ከመጠቃታቸው በፊት ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል።

እንደ አገርም በጋራ የስምጥ ሸለቆ ተፈጥሮ ሐይቆችና የተፋሰስ ሀብቶችን የጥበቃ ሥራውን በማስቀጠል በተፋሰስ ልማት ምርት ለማምረት፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ በሀይድሮ ኤሌክትሪክ የኃይል ምንጭነት በመጠቀም የኢነርጂ ፍላጎትንና ዋስትናን ለማሟላትና ለማረጋገጥ የግድ የተጠበቀና አስተማማኝ የውሃ ሀብት ሊኖረን ይገባል ያሉት አማካሪው፣ ሐይቆችን በመጠበቅ፣ በመንከባከብ፣ በመከታተልና በዘላቂነት ሳይጎዱ እንደተጠበቁ እንዲቀጥሉ ለማድረግ በጋራ ፣ በኃላፊነትና በህጋዊ መንገድ በመጠቀም መጠበቅ እና ማልማት እንደሚገባም ገልጸዋል።

የመጠጥ ውሃ ዋስትናን ለማረጋገጥ የጠራ ውሃ በበቂ መጠን ሊኖረን ይገባል ያሉት አማካሪው፣ በዚህ ረገድ



አቶ አስማማው ቁሜ

ወደፊት የሚጠብቁን ብዙ ነገሮችና ሥራዎች ናቸው ብለዋል።

እንደ አገርም በውሃና ኢነርጂ ስር ያሉት ተፋሰስ ጽህፈት ቤቶችም ሰፋ ያለ የአስርና አሥራ አምስት ዓመት ሊተገበር የሚችል የተፋሰስ ልማት እቅድ ማዘጋጀትና ማህበረሰቡን በማስገንዘብ የስምጥ ሸለቆ የተፈጥሮ ሐይቆችና የተፋሰስ ሀብቶችን እራሱ ጠባቂ፣ ተጠቃሚም እንዲሆን በማነቃነቅ ጭምር መስራት አለባቸው ብለዋል።

እቅዱም በውሃ ምደባ፣ በውሃ ታሪፍ ስርዓት፣ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ሥራ ሊያሰሩ የሚችል አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥን ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር በመፍጠር እየተሰራ ነው ያሉት አማካሪው፤ ይህ በየአካባቢው ባሉት ጽህፈት ቤቶች ሊጠናከር ይገባል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የስምጥ ሸለቆ ሐይቆችና የውሃማ አካላት አስጊ ደረጃ ላይ ናቸው ያሉት አቶ አስማማው፣ የስምጥ ሸለቆዎችንና የውሃማ አካላት ጥበቃና አስተዳደሩ ላይ አተኩሮ መስራት ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

ለጥበቃ ሥራውም ሕዝብን ማስተባበር፣ አጠቃቀሙን መቆጣጠር ፣ መከታተል፣ እንዴት አድርገን ሁል ጊዜ እየቃኘን ከስጋት ነጻ እንዲሆኑ ማድረግ ከሌሎች አገሮች ልምድና ተሞክሮ መውሰድ ያስፈልገናል ሲሉም ተናግረዋል።

በጣና ሐይቅ ላይ በተከሰተው መጤ አረሞች በሐይቁ ከልማቱ ይልቅ ምን ያህል የሰው ኃይል መከላከል ሥራ እንደዋለ፣ ምን ያህል ፋይናንስ ወጪ እንደተደረገና እንደባከነ ይታወሳል ያሉት አቶ አስማማው፣ አሁን ችግር ከመድረሱ በፊት ጥበቃው ላይ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል። በእነሱ ላይ የሚሰሩትን ልማቶችም አብሮ ለመጠበቅ ጥበቃውን ማስቀደም አስፈላጊ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

## የባለሙያዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ደንቦችን አውቀው እንዲሰሩ መደረጉና ግብር ከፋዮች መብትና ግዴታቸውን አውቀው ግብር መክፈል እንዲችሉ መደረጉ፤ በተበታተነ መንገድ የነበረውን የተገልጋዮችን ቻርተር መልክ በማስያዝ በሰነድ ቅርጽ በማስያዝ ለግብር ከፋዮች እንዲደርስ መደረጉ፣ ግብር ከፋዮች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በየቅርንጫፍ ቢሮዎችና የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰራታቸው አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ አገልግሎት አሰጣጡ ዘመናዊ እንዲሆን ባለፈው በጀት ዓመት «ኢቲ ታክስ» የሚባል የዲጂታል አሰራር ሲስተምና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር በቴሌ ብር አማካኝነት መክፈል እንዲቻል ተደርጓል። ይህም ከዚህ በፊት የነበረውን አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ አንጻር በግማሽ የሚቀንስ ነው። በተጨማሪም እንደ መዘግየት ሌብነትና የሚታዩ ማጭበርበሮችን ሊቀርፍ የሚያስችል ነው። እነዚህንና መሰል የአይሲቲ ሥራዎች በመሰራታቸው አፈጻጸሙ ከፍ እንዲል አድርጓል። የቅንጅት ሥራዎችን ለማቀላጠፍ ከተለያዩ ባለድርሻ ተቋማት ጋር የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ወደ ተግባር መግባቱን ገልጸዋል።

የህግ ማስከበር ሥራው ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ በመሰራቱ ታክሳቸውን በአግባቡና በወቅቱ በማያሳውቁት ላይ ክትትል በማድረግ፣ ከህሰተኛ ደረሰኝ ጋር ያሉ ችግሮችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እርምጃዎች መወሰዳቸውን ገልጸዋል።

በዚህ ዓመት በገቢዎች ቢሮ ብቻ ገቢ ለመሰብሰብ የተቃደው 70 ቢሊዮን ብር መሆኑን የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ አጠቃላይ ከተማ አስተዳደሩ በጀት ብሎ ያወጀው 100 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ነው። ከዚህ ውስጥ በገቢዎች ቢሮ የሚሸፈነው 70 ቢሊዮን ሲሆን ቀሪው ታክስ ያልሆኑና በማዘጋጃ ቤታዊ ገቢዎችና በሌሎች ተቋማት የሚሸፈኑ ናቸው።

ዋናው የግብር መክፍያ ወቅት ከሐምሌ አንድ እስከ ጥቅምት 30 ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑን የገለጹት አቶ ሙሉጌታ፤ የዓመቱን 42 በመቶ የሚሆነው ገቢ በአራቱ ወራት ለመሰብሰብ ታቅዷል ብለዋል። ቀሪው የደመወዝ ገቢ ግብር፤ የቤት ኪራይ ገቢ፣ የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ፤ ቲኦቲ፣ ኤክሳይስ ታክስ፣ ቫት፣ የመሳሰሉት በመደበኛነት የሚሰበሰቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ከኢቲ ታክስ በተጨማሪ የአከፋፈል ሂደቱን ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆን ለማስቻል ግብር ከፋዮች ካሉበት ቦታ ሆነው ከፍያ እንዲከፍሉ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ስምምነት በመፈራረም የቴሌ ብር አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል። ግብር ከፋዩ የትኛውም ቦታ ሆኖ በቀላሉ ካለው አካውንቱ ላይ ወደ ቴሌ ብር አካውንት ገንዘብ የማስተላለፍና ግብር ሲከፍል ወዲውኑ ክሪላንስ የሚያገኝበት አሰራር መመቻቸቱን የቢሮ ኃላፊው ገልጸዋል።

ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር ተያይዞ ኔትወርክ ችግር እንዳያጋጥም ከቴሌ ጋር በመነጋገር ትልልቅ ሰርቨሮችን በመጠቀም መጉላላት እንዳያጋጥም እየተሰራ ነው ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ለግብር አሰባሰቡም የንቅናቄ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

## «አገልግሎትን በገንዘብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በኋላ ወይም የህዝብ ንብረት ሰርቀው ከተካፈሉ በኋላ ወደ ሚዲያ ማምጣት ወይም ቅሬታ ማቅረብ ማንንም አይጠቅምም። ይልቁንስ ለደረጃ እድገትና ወይም ለሥራ ቅጥር ጉቦ የጠየቀውን አካል ወዲያዉኑ በማጋለጥ ወደ ህግ ማቅረብ ነው። ራስንና አገር መታደግ ብሎም የክፋት ምንጭ ማድረቅ ይሄ ወሳኙ እርምጃ ነው።

ከወራት በፊት በብልጽግና ፓርቲ የመጀመሪያው ጉባዔ መንግሥት ቁልፍ አገራዊ ችግሮች ለአብነትም የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች፣ የልማትና የሰላም ጉዳዮች በመለየት አቅጣጫ ማስቀመጡን ያነሱት ዶክተር ቢቅላ፣ ችግሮቹን ለመቅረፍ በየደረጃው ያሉ የፌዴራልና የክልል አመራሮች ባደረጉት እንቅስቃሴ በመልካም አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በልማት ሥራዎችና በሰላምና ረገድ መሻሻሎች መታየታቸውን ገልጸዋል።

እነዚህ ችግሮች በጥናት የተለዩ የአገር ህልውና ለማስቀጠል ወሳኝ ጉዳዮች በመሆናቸው መንግሥት ለችግሮቹ አጽንኦት ሰጥቶ እየሰራ ነው ያሉት አስተባባሪው፣ከዚህ አንጻር አገሪቱን የብጥብጥ ቀጠና ለማድረግ ተንሰፍስፈው የነበሩ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ሴራ ማክሸፍ መቻሉንና በየመሥሪያ ቤቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍጠር፣አገልግሎትን በገንዘብ በመሸጥና በሌብነት የጠላቶቻችን ተባባሪ የሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ አመራሮችና ሰራተኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን ጠቁመዋል።

ምንም እንኳ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለዘመናት ሥር የሰደዱ ችግሮች በመሆናቸው በአንዴ አመርቂ ለውጥ ማምጣት ባይቻልም ለወደፊትም የመንግሥት ቀዳሚ ትኩረት ናቸው ያሉት ዶክተር ቢቂላ፣ አሁን ላይ የተገልጋዮችን እንግልት ለማስቀረት በሁሉም ክልሎች የመሥሪያ ቤት ሥራ ኃላፊዎች በሳምንት ሁለት ወይም ሶስት ቀናት ቢሮ በመሆን ደንበኞችን በቀጥታ እንዲያገለግሉ የተወሰነ ውሳኔ ውጤታማ መሆኑንና ሌሎችም በሂደት ለማስተካከል ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

አገሪቱ ፍጹም እንዳትረጋጋ ጠላቶች በየአካባቢው ሽብር ለመፍጠር ያደረጉት ሰፊ ዝግጅት በተባበረ ክንድ በማክሸፍ አገር ማስቀጠል መቻሉን የገለጹት አስተባባሪው፤ ከተገልጋዮች ጉቦ ከመቀበል፣ ደንበኞችን ከማጉላላትና ከሌብነት የነበሩ ችግሮች ላይ መሻሻሎች ቢኖሩም በሚፈለገው ልክ ውጤት ስላልመጣ በቀጣይም የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል።

## «ሶስተኛ ወገን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የወጡ አንዳንድ መሪዎቻቸው የሌሎች ሃገራትን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ ተፈጻሚ ማድረግ ይፈልጋሉ። ይህም የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነኩ ደባዎችን በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ላይ ሲፈጽሙ መቆየታቸው ማሳያ ነው።

ድርጊቱ ከኢትዮጵያ ጋር ለረጅም ዘመናት መልካም ግንኙነት ያለውን የሱዳን ሕዝብ የሚመለከት ሳይሆን የሌሎችን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን የሚፈልጉ ቡድኖች በተለይ ከጦር አበጋዞች ጋር እንደሚያያዝ ገልጸዋል።

በሱዳኖች የተደረገው ደባ በአጠቃላይ ሲታይ የሌላ ሶስተኛ ወገን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን የተደረገ ድርጊት መሆኑን አስታውሰው ኢትዮጵያ ግን ለሱዳናውያን ወንድሞች ሰላምና መረጋጋት የበኩሏን አስተዋጽኦ ስታበረክት ቆይታለች ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር አደም ገለጻ እ.አ.አ በ2010 ዓ.ም በጀኔራል ኡመር የሚመራ ኦፕሬሽን እና የሆስኒ ሙባረክ ግድያ ሙከራ በኢትዮጵያ መካሄድ የራሱ ምክንያት አለው። ሌላው ጥቅምት 24 የሰሜን እዝ በህወሓት ጦርነት ሲከፈትበት በኢትዮጵያ መከላከያ ላይ ክፍተት ይፈጠራል በሚል ግምት በኢትዮጵያ ላይ ዘምተዋል። እነዚህ ቡድኖች ህወሓትን አስታጥቆ ወደ ኢትዮጵያ የመላክ ሥራዎችንም ሰርተዋል። በቀይ ሽብር ዘመን በሱዳን ውስጥ ኤጀንሲ በመክፈት በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር በመፈጸም ኢትዮጵያን ዘርፈዋል።

እነዚህ ሃይሎች የኢትዮጵያ ታሪኮችን የራሳቸው በማድረግ የታሪክ ዘረፋም አካሄደዋል ያሉት፣ በተለይ ኢትዮጵያ ካሏት እስላማዊ ታሪኮች ውስጥ የእነ ቢላል እና ነጃሺ መስጅድ ታሪኮችን የራሳቸው ታሪክ በማስመሰል መጽሐፍትን በማሳተም ሲሸጡ መቆየታቸውን ገልጸዋል።

ከሕዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ የሌሎችን ፍላጎት ማዕከል ባደረገ መልኩ ለጸጥታው ምክርቤት ለአፍሪካ አንድነት ወዘተ የተለያዩ ደብዳቤዎችን በመጻፍ አጀንዳ በመፍጠር ኢትዮጵያን ጥቅም ለማሳጣት ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል ብለዋል።

ከዚህ ሁሉ የሱዳን ገዢዎች ድርጊት በስተጀርባ ሶስተኛ ወገን እንዳለ ኢትዮጵያውያን መረዳት ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር አደም ሰላምን በማረጋገጥ ውስጣዊ አንድነት በማጠናከር አሸንፎ መውጣት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

ለዚህ ሁሉ ሴራቸው ስኬት የግብፅ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወደ አረብ ሊግ ሲመላለስ መቆየቱን የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር አደም፤ ኢትዮጵያም ጠንካራ የውጭ ዲፕሎማስ መስራት እንደሚጠበቅባት ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በጋራ መኖሪያ ቤቶች ማስተላለፍ ላይ የተዓማኒነት ጉድለት እንዲፈጠር ያደረጉ ግለሰቦች ላይ አስተማሪ ርምጃ ይወሰድ!

መንግሥት በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማሟላት ከቀየሳቸው ስልቶች መካከል የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ለነዋሪው በዕጣ ማከፋፈል አንዱ ነው። በዚሁ አሰራርም በ1995 የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ ግብርን በማስጀመር የመጀመሪያዎቹን ቤቶች በገርጂ አካባቢ ገንብቶ በእጣ ለነዋሪዎች አከፋፍሏል። እስከ አሁንም ድረስ 300ሺ የሚጠጉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለነዋሪዎች መተላለፋቸውን ከቤቶች ኤጀንሲ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ይሁን እንጂ የመኖሪያ ቤት ፍላጎትን በማቃለል ረገድ ተስፋ የተጣለበት የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ ግብር በበርካታ ብልሹ አሰራሮች የታጠረ እና ለሌብነትና ብልሹ አሰራር የተጋለጠ ሆኖ ኖሯል። በዋነኝነትም በቀደመው የኢህአዴግ አስተዳደር ለስርዓቱ ደጋፊዎችና ቤተሰቦች የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለአጉል መጠቃቀም እና ብልሹ አሰራር በር የከፈቱ ነበሩ። ለግለሰቦች የተለየ ቅርበት ያላቸውና በጥቅም የተሳሰሩ ሰዎች በቤት ፈላጊነት ተመዘገቡም አልተመዘገቡም የጋራ መኖሪያ ቤት ባለቤት ከመሆን የሚያግዳቸው እንዳልነበረም ብዙ ተብሏል።

በወቅቱ የነበረው የኢህአዴግ አስተዳደር በ1997 ዓ.ም ለቤት ፈላጊዎች ጥሪ አድርጎ ከ450ሺ በላይ የከተማዋን ነዋሪዎች መዝግቧል። በተመሳሳይም በሁለተኛ ዙር በ2005 ዓ.ም ከ1ሚሊዮን በላይ የከተማዋን ነዋሪዎች በመመዝገብ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ለማዳረስ ቃል ገብቷል። ሆኖም በነበረው የጥቅመኝነትና የሙስና ብልሹ አሰራር በርካታ ዜጎች ጊዜ ከመቁጠር በዘለለ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እንደሰማይ ርቀዋቸው ቆይተዋል።

በወቅቱ የነበረው አገዛዝ በልዩ ጥቅም የተሳሰሩትንና ቅርበት ያላቸውን ሰዎች ለመጥቀም የሚያስችል የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ዕጣ ማውጫ ሶፍትዌር በማበልጸግ ኢፍትሃዊ በሆነ መልኩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለማይገባቸው ሰዎች ሲያድል መኖሩም ብዙዎች የሚናገሩት ሀቅ ነው። በመንግሥት ደረጃ ድጋፍ በማድረግም የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ዕጣ ማውጫ ሶፍትዌርን የሚያበለጽጉ ግለሰቦችን በመቅጠር ከምዝገባ ውጪ ያሉ ሰዎች በእጣው ውስጥ እንዲካተቱ አንዳንዶቹም ስለኮንዶሚኒየም ምንም ግንዛቤ የሌላቸው ሁሉ ከተለያየ ቦታ እየተጠሩ በገፍ እንዲታደላቸው ተደርጓል።

ይህ ኢፍትሃዊ አካሄድ ከ1ሚሊዮን በላይ የሆነውን ቤት ፈላጊ ዜጋ ተስፋ ከማስቆረጡም በላይ በነበረው የኢህአዴግ ስርዓት ላይ እምነት እንዲያጣ አድርጓል። በርካቶችም በዚህ ምክንያት የቆጠቡትን ገንዘብ ከባንክ በማውጣት ተስፋ ቢስ ሕይወት ለመኖር ተገደዋል። ጥቂቶች ግን ከዛሬ ነገ ሁኔታዎች ሊለወጡ ይችላሉ በሚልም ለ17 ዓመታት ያህል በተስፋ ኖረዋል።

ሐምሌ 1 ቀን 2014 ለአስራ ሰባት ዓመታት በተስፋ ለኖሩት ቤት ጠባቂዎች የተለየች ቀን ነበረች። ምኞታቸው የሚሳካበት፤ ተስፋቸው የሚለመልምበት ቀን መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ ባለስልጣናት አማካኝነት ተበሰረ። በ1997 እና በ2005 የተመዘገቡና በአግባቡ የቆጠቡ ከ73ሺ በላይ ነዋሪዎች በዕጣ ውስጥ ተካተው እንደሚወዳደሩ ተነገረ ። 25ሺ 491 ቤቶችም ለባለዕድለኞች በዕጣ እንደሚተላለፉ ተገለጸ። ይህቺ ቀን ብዙዎች በጉጉት የጠበቋት ቀን ነችና ተደሰቱ።

ሆኖም ጣጣ የማያጣውና በሙስናና በብልሹ አሰራር የተተበተበው የጋራ መኖሪያ ቤቶች የዕጣ አወጣጥ ስነስርዓት መርዶ ይዞ መጣ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሐምሌ 01 ቀን 2014 በወጣው የ20/80 እና 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕጣ የዳታ ማጭበርበር ድርጊት በመከሰቱ ታወጀ። ይህ ሁኔታ ብዙዎችን አስደነገጠ፤ ተስፋ ሰንቀው የነበሩትን ዜጎች ዳግም ጽልመት ውስጥ ከተተ።

ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ የከተማ አስተዳደሩ መግለጫ አውጥቷል። የከተማ አስተዳደሩ ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው ከዕጣ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት በኋላ የተለያዩ ጥቆማዎች በመቅረባቸው የኦዲት ሥራ ሲጀመር ከባንክ የተላከውና ለእጣ እንዲውል ወደ ኮምፒዩተር የተጫነው ዳታ ልዩነት ተገኝቶበታል።

በእስካሁኑ የማጣራት ሥራም ላልቆጠቡ ሰዎች እጣ መውጣትን ጨምሮ የተለያዩ የተዓማኒነት ጉድለቶች መታየታቸውንና በጉዳዩ የተጠረጠሩ ባለሙያዎች እና አመራር በቁጥጥር ሥር ሆነው ምርመራ እየተደረገ መሆኑን ነው የገለጸው።

አስተዳደሩ ጉዳዩን ደርሶበት ቶሎ ማስቆሙና በተቻለ መጠን ጉዳዩን ለህዝብ ይፋ ማድረጉ መንግሥት ፍትሃዊ አሰራር እንዲሰፍን ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነውና ይበል የሚሰኝ ነው። ሆኖም አሁን ካለንበት የለውጥ ዕሳቤ አንጻርና በተለይም ተቋማት ከአድሎና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው እንዲሰሩ መሰረት እየተጣለበት ባለበት ወቅት ይህ መሰል መርዶ መሰማቱ አሁንም መንግሥት ተቋማቱንና ሕዝብ እንዲያገለግሉ የመደባቸውን አመራሮቹን መለስ ብሎ መፈተሽ እንዳለበት የሚጠቁምም ነው።

የጥቂት ግለሰቦችን ኪስ ለማደለብ ሲባል ብዙሃኑን ህዝብ እያሳዘኑ መቀጠል ጊዜው የሚፈቅደው ባለመሆኑ በሕግ አግባብ በወንጀል ፈጻሚዎቹ ላይ ጠበቅ ያለና አስተማሪ እርምጃ መውሰድም ይገባል። ይህ ሲሆን የትላንት ጠባሳው ያልሻረለትና ከእለት ጉርሱ ቀንሶ ለበርካታ ዓመታት ሲቆጥብና በከፍተኛ ጉጉት ሲጠባበቅ ለኖረው ቤት ፈላጊ ህብረተሰብም የቁስሉ መዳኛ መድኃኒት ይሆናል። በቀጣይም ለተመሳሳይ ድርጊት የቋመጡ ግለሰቦች እጃቸው እንዲሰበሰብ ያደርጋል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

# የነገር መመዘኛችን ምንድን ነው?

**ዶክተር ጀኔኑስ**

ነገሮች ማነፀሪያ እና ዋጋ ከሌላቸው ዓለም ከንቱ ናት። ይህን ለማወቅ ጊዜ እና ሁኔታን ማገናዘብ ተገቢ ነው። ይህን መግቢያ ሐሳብ ያጠናከርልኝ ዘንድ ይህን ተረት ልጠቀም ተገደድኩኝ።

ከዕለታት ባንዱ ቀን አንድ ታዳጊ አባቱን ‹‹የህይወት ዋጋው ስንት ነው?›› ሲል ጠየቀው። አባትም መልስ በመስጠት ፈንታ ልጁን እንዲህ ሲል አዘዘው። ‹‹እንካ ይህንን የድንጋይ ቁራጭ…ወደ ገበያ ውሰደው። ሰዎችም ዋጋውን ከጠየቁህ በጣቶችህ ሁለት ቁጥርን ብቻ አሳያቸው እንጂ ምንም አትናገር›› አለው።

ልጁም ድንጋዩን ወሰደ። ወጥቶም በገበያ መሃል ቆመ። አንዲት ሴትም መጣች። ‹‹ይህ ድንጋይ ዋጋው ስንት ነው? ብትሸጥልኝ ወስጄ ግቢዬ ውስጥ አስቀምጠዋለሁ›› አለችው። ልጁም እንደታዘዘው ምንም ሳይናገር ሁለት ጣቶቹን አሳያት። እሷም አለች ‹‹ሁለት ብር? እወስደዋለሁ›› ልጁም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

በገበያ ያጋጠመውንም ለአባቱ ነገረው። አባትየውም አለው ‹‹አሁን ደግሞ ድንጋዩን ይዘህ ወደ ሙዚየም ሂድ። ዋጋውን ሲጠይቁህም ሁለት ጣቶችህን አሳይ››አለው። ልጁም ወደ ሙዚየም ወጣ። ገዢም መጥቶ ዋጋ በጠየቀው ጊዜ ሁለት ጣቶቹን አሳየው። ገዢውም ‹‹ሁለት መቶ ብር? እወስደዋለሁ!›› አለው። ልጁም በድንጋጤ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ያጋጠመውንም ለአባቱ ነገረው።

አባትየውም ተናገረ፤ ‹‹አሁን ደግሞ በመጨረሻ ድንጋዩን ይዘህ ወደ የከበሩ ማዕድናት መሸጫ ሂድ ለባለቤቱም አሳየው›› አለው። ልጁም ሄደ። ለሱቁም ባለቤት አሳየው። የሱቁ ባለቤት በመገረም ‹‹ይህ እኮ አለም ላይ እጅግ ውድ ከሆኑ የከበሩ ድንጋዮች አንዱ ነው›› አለ። ‹‹ከየት አገኘኸው? ስንትስ ትሸጠዋለህ?›› ሲል ጠየቀው። ልጁም ምንም ሳይናገር ሁለት ጣቶቹን አሳየ። የሱቁም ባለቤት ‹‹ይህንን ድንጋይ 200ሺ ብር እወስደዋለሁ››አለው፤ ልጁም በመገረም እየሮጠ ወደ ቤቱ ተመልሶ ያጋጠመውን ለአባቱ ነገረው።

አባትየውም ‹‹ልጄ አሁን የህይወትህ ዋጋ ተገልጦልሃል›› አለው። አየህ የመጣህበት ቦታ፣ ዘርህ፣ ሃይማኖትህ፣ የቤተሰቦችህ ሃብት፣ የተወለድክበት ቦታ ልዩነት አይፈጥርም። ዋናው ራስህን የምታስቀምጥበት ቦታ፣ ራስህን የምታገኝበት የሰዎች ስብስብ ነው። ልዩነቱ ያለው ራስህን ለመሸከም በምትመርጥበት መንገድ ነው። ህይወትህን ሙሉ የሁለት ብር ድንጋይ ዋጋ ስትሰጠው ኖረህ ይሆናል።

ህይወትህን ሙሉ የኖርከው ዋጋህ ሁለት ብር ብቻ እንደሆነ በሚያስቡ ሰዎች ተከበህ ይሆናል። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ውድ የሆነ የከበረ ድንጋይ በውስጡ ይዟል። ልዩነቱም ያለው ውስጣችን ያለውን የከበረ ድንጋይ አይተው ዋጋ በሚሰጡን ሰዎች መሃል መገኘትን ስንመርጥ ነው። ራሳችንን በገበያ ወይም በከበሩ ማዕድናት ሱቅ የማስቀመጥ ምርጫው አለን።

በሌሎች ሰዎች ውስጥ ያለውንም ውድ ዋጋ ለማየት ምርጫው የኛው ነው። ሌሎች ሰዎችም የከበረ ዋጋቸውን እንዲረዱ ማድረግ እንችላለን። አብረህ የምትውላቸውን ሰዎች በጥንቃቄ ምረጥ። ይህ በህይወትህ ልዩነትን ይፈጥራል ሲል ልጁን መከረው ይባላል።

ይህን አጭር መግቢያ ተረት መሰል ግን ቁምነገር አዘል አባባል ለመጠቀም ያስገደደኝ የአገራችን ሰሞንኛ ጉዳዮች ናቸው። በርካቶቻችን ለአንዳንዶች ምንሰጠው ዋጋ እና እነርሱ ለራሳቸው የሚሰጡት ዋጋ አለመጣጣሙ ብዙ ኪሳራ ወይንም ምንም ትርፍ የሌለው ሆኖ እናገኘዋለን።

ለዘመናት ሥናቀነቅን የነበረው የዘረኝነት፣ መንደሬነትና የዘውጌ ፖለቲካ ኢትዮጵያን ክፉኛ አጎሳቁሏታል፤ ከባድ ህመም ውስጥ ከቷተል። የእነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያን ያለቦታው እንደተቀመጠ እንቁ አድርገዋታል። በተለይም አሸባሪቹ ሸኔ፣ ሕወሓት፣ ጽንፈኛው የቅማንት ቡድን እና በአንዳንድ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ ኢ-መደበኛ ኃይሎች የኢትዮጵያን ልክ መረዳት አልቻሉም፤ መረዳትም አይፈልጉም።

አሸባሪው ሕወሓት በአምሳሉ የፈጠራቸውን በሙሉ በአይዞህ ባይነት ወደመጥፎ አረንቋ ነው የወሰዳቸው። ‹‹ግም ለግም ተያይዘህ አዝግም›› እንደሚባለው፤ ሁሉም ተያይዘው ገደል እየገቡ ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ጠላት እየወጉ የምንታገለው ለአንተ ነው ብለው ሊያሞኙ ይፈልጋሉ።

ዘረኝነትና ተረኝነትን ከሚገባው በላይ ሲያጋግል የቆየውአሸባሪው ሕወሓት በመጨረሻ እራሱ ተለብልቦበታል። ለሕወሓት የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት በሚገባው ቋንቋ አነጋግረውት ተገቢውን አግኝቷል ።

አለውልህ የሚለውን ህዝብ በርሃብ አለንጋ እንዲገረፍ እሱ በለኮሰው ጦርነት ከፍ ያለ ዋጋ እንዲከፍል አድርጎታል። አሁንም ከዚህ የሕወሓት የውርደት ሞት ያልተማሩ ፀረ-ሠላም ኃይሎች ኢትዮጵያን እየወጉ መጀገን ይፈልጋሉ።

እናቱን ከኋላ እየወጋ ጀብደኛ የተባለ አልሰማንም፤ አላየንም ወደፊትም አይኖርም። የሕወሓትን ዋጋ የሚያውቅ አካል በዚያው ልክ ለመለካት መሞከር በእጅጉ አሳፋሪ ለውድቀትና ውርደት መዘጋጀት ነው። ሸኔ እና መሰሎቹም ምኞት ይኸው ነበር።

ሸኔ ከኤርትራ በርሃ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስና በአገሩ እንዲንቀሳቀስ እድል፤ ክብርና ፍቅር ቢሰጠውም ‹‹ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ ሆኖ›› ኢትዮጵያን ከውስጥ ሆኖ እያደማት ነው። ሰንጋ አርደው እልል ብለው የተቀበሉትን ወገኖቹን እየገደለ፤ እየዘረፈ፤ እየደፈረና እያሳደደ ነው።

ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በሠላማዊ መንገድ እንዲታገል ሲፈቀድለት አሻፈረኝ ብሎ የድል አጥቢያ አርበኛ ሆኖ ኢትዮጵያን እያደማት ነው። ኢ-መደበኛ ሃይሎችም መንግስትን እገዳደራለሁ ብለው ቡራ ከረዮ እያሉ ነው። ዳሩ ግን ይህ ልፋታቸውና የክፉ አመል ፖለቲካቸው ገደል እያስገባቸው ነው። እንኳንስ መንግስትን መገዳደር ቀርቶ በአንዲት ትንሽ መንደር ተቀባይነት አጥተው እንደ እብድ ውሻ እዚህም እዚያም እየተክለፈለፉ ነው።

ከእውነታው መረዳት የሚቻለው ርካሽ ሆነው በውድ የገመትናቸው እነዚህ የድል አጥቢያ ኃይሎች የሚጀምሩት እንጂ የሚፈፅሙት ትግል የለም። የሚመኙት እንጂ የሚዘልቁበት ወይንም የሚቆናጠጡት ስልጣን የለም። የሚያደሙት እንጂ የሚጠቅሙት ህዝብ የለም።

ከእነዚህ ኃይሎች ወቅታዊ ቁመና እና እሳቤያቸው አንድ ነገር መረዳት ይቻላል። ርካሽ ሆነው ሳለ እኛ እንደ ውድ ቆጥረናቸው ቆይተናል። እነዚህ አካላት ልክ ከላይ እንደተጠቀሰው ምሳሌ ናቸው። ከመጀመሪያውኑ ዋጋቸውን በደንብ ሳንረዳ በጣም የካብናቸው ናቸው። እንደከበረ ማዕድን ስናያቸው የነበሩቱ አሁን ዋጋቸው ከሚዛኑ ወርዷል።

ቀድሞውኑ ያለቦታቸው ማስቀመጥና መመዘን አልነበረብንም። በወርቅ ሚዛን ስንለካቸው የነበረው ከአመድ አንሰው መገኘታቸውን ከግብራቸውና ምግባራቸው መረዳት ይቻላል። ልክ ታዳጊው የህይወትን ዋጋ ለመረዳት እንደተንከራተተው እኛም የእነዚህን አካላት ዋጋ ለማወቅ ዘግይተን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጊዜ እውነተኛ መነጽር ነውና የእነዚህ የእናት ጡት ነካሾችን ዋጋ አሁን ለመገንዘብ በቅተናል፤ በፀረ ኢትዮጵያ አቋማቸው።

እነሱን ለማወቅ ያጠፋነው ጊዜ ሊቆጨን አይገባም፤ ከአሁን በኋላ ለሚመጣው መዘጋጀት እንጂ። በመሆኑም እነዚህ አካላት ዋጋቸውን ሰቅለን ከሆነም በልኩ ልንመዝናቸው፤ ያለቦታቸው አስቀምጠን ከሆነም ወደሚገባቸው ቦታ መመለስና የእነርሱን እውነተኛ ዋጋ እና ምስል ማሳየት አለብን።

ይህ የሚሆነው ደግሞ እንደ ጀበደኛ እና እንቁ የሰቀልናቸው ከትቢያ ያነሱ ስለመሆናቸው በሚገባ በማሳየት ነው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ዋጋቸው ስንት ነው በሚል የተቃለለ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ከምንም የማይቆጠሩ መሆናቸውን በእውነተኛ ትግል ዋጋቸውን በማሳነስና ሀቁን በማስቀመጥ ነው።

# ትምህርት ቤትን ወደ መጠጥ ቤት በማዞር የተፈጠረ ውዝግብ

**ሙሉቀን ታደገ**

የዛሬው የ‹‹ፍረዱኝ›› አምድ ዝግጅታችን በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በሚገኙት ሁለት የአጸደ ህጻናት ትምህርት ቤቶችን ይመለከታል። አጸደ ህጻናቱ ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እና አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት በመባል ይታወቃሉ። በአፀደ ሕፃናቱ የሚያስተምሩ መምህራን ለቅሬታቸው መነሻ የሆነውን ምክንያት ይዘው ወደ ዝግጅት ክፍላችን መጥተዋል። ቅሬታው የተፈጠረው በትምህርት ቤቱ እና በሸማች ህብረት ስራ ማህበር መካከል ሲሆን ‹‹በድል ተፈጽሞብናል›› ሲሉ አቤቱታ ያቀረቡት የህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እና አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት መምህራን ናቸው። ከቅሬታው ጋር ተያይዞም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ምላሽም አካተን እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።

«በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኘው የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር በ2004 ዓ.ም በአደራ ከተረከባቸው ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነው ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት ማስተማሪያ ህንጻ ወደ መጠጥ ቤት በመቀየር ተማሪዎችን ከመበተኑ ባለፈ መምህራንንም ለአልተጋባ እንግልት ዳርጎል። » የሚሉት መምህራኑ፤ ይሄው ሸማች ማህበር በአደራ የተረከበውን የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት የሚያስተምሩ መምህራንን ጥቅማ ጥቅም በመከልከል እና መምህራንን አሰላችቶ ትምህርት ቤቱን ለቀው እንዲሄዱ በማድረግ የትምህርት ቤቱን ህንጻ ላልተገባ ጥቅም ለማዋል በማሰብ በደል ሲፈፅም መቆየቱን በምሬት ይገልጻሉ።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ከሰዎች እና ከሰነዶች ያገኛቸውን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ ግራ እና ቀኙን በማየት መፍረድ ይችል ዘንድ የውዝግቡን ክፍል አንድ የምርመራ ሂደት እነሆ ብለናል።

በትምህርት ቤቶቹ አቤቱታ ያቀረቡ መምህራን በርካታ ናቸው። ይሁን እንጂ የሁሉም መምህራን አቤቱታ አንድ አይነት ስለሆነ ህጻን ዓለም እና አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናትን የሚወክሉልን ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች አንድ አንድ መምህራን ጋር ቃለ ምልልስ አድርገናል።

የመጀመሪያዋ አቤቱታ አቅራቢ መምህርት ዓለም ጌታቸው ይባላሉ። በህጻን ዓለም ትምህርት ቤት ለ30 ዓመታት ያህል መስራታቸውን ይናገራሉ። እንደ መምህርቷ ገለጻ፤ ከ2004 ዓ.ም በፊት ህጻን ዓለም ትምህርት ቤት የሕዝብ ትምህርት ቤት ነበር። ነገር ግን በ2004 ዓ.ም በወጣው መመሪያ መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ እና ሕዝብ ያስተዳድራቸው የነበሩ ትምህርት ቤቶች በመንግስት አስተዳደር ስር እንዲሆኑ ተወሰነ። ይህን ተከትሎ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ይገኙ የነበሩ በርካታ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መንግስት እንዲያስተዳድራቸው ወደ መንግስት ትምህርት ቤት ተዘዋወሩ።

ይሁን እንጂ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ከሚገኙ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እና የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት አልተካተቱም፡፡ ይልቁንም ባልታወቀ ምክንያት ለሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር በአደራነት ተሰጡ። ትምህርት ቤቶች ለማስተዳደር በአደራ የተቀበለው አካልም ስለሙያው ግንዛቤ የሌላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ እያደር የትምህርት ቤቱ ህልውና ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ መምጣቱን ይናገራሉ።



መምህርት ዓለም ጌታቸው፤



መምህርት አንጓች ታደሰ፤

**በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ከሚገኙ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መካከል ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እና የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት አልተካተቱም፡፡ይልቁንም ባልታወቀ ምክንያት ለሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር በአደራነት ተሰጡ**

መምህራኑ በትምህርት ቤቱ መምህራን እና ህጻናት የሚፈጸሙ ሁሉም አስተዳደራዊ በደሎች ከነገ ዛሬ ይሻሻላሉ በማለት በተስፋ እየሰሩ ቢቆዩም፤ የወረዳ 6 የሸማች ማህበር የህጻን ዓለምን አጸደ ህጻናትን ህንጻ ለማደስ በሚል ሰበብ መምህራን ሙሉ ተማሪዎቻቸውን ይዘው ወደ አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት እንዲቀላቀሉ መደረጉን አቤቱታ አቅራቢዋ ያስረዳሉ።

ወደ አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ተደርበው እንዲሄዱ ሲደረግ የትምህርት ቤቱ ህንጻ የቤቱ እድሳት እስከሚያልቅ ተብለው እንደነበር ያስታውሳሉ። ይሁን እንጂ የህንጻው እድሳት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ነበሩበት ህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት እንዲመለሱ ጥያቄ ቢያቀርቡም ጥያቄያቸው ሰሚ አጥቶ ለዓመታት ትውልድን ሲቀረጽበት የነበረው ትምህርት ቤት ለመጠጥ ቤት አገልግሎት እንዲውል መደረጉን ያብራራሉ።

ሆኖም ግን እስካሁን ድረስ ደመወዝ የሚከፈላቸው በህጻን ዓለም ትምህርት ቤት ስም ነው። ለመከላከያ እና መሰል አገራዊ ግዳጆች መዋጮ የሚያደርጉትም በዚሁ በኩል ነው። ‹‹ሌላው ደግሞ›› ይላሉ መምህርቷ በአንድ ከተማ አስተዳደር ስር እየሰሩ ለመምህራኑ የሚከፈለው ደመወዝ በመንግስት ትምህርት ቤት ከሚሰሩ መምህራን እጅጉን ያነሰ ነው። የመምህራን ጥቅማ ጥቅም የሚባለው ነገር ፈጽሞ እንደማይታሰብ ያስረዳሉ። እንደ መንግስት መምህራን የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸው እና ጥቅማ ጥቅሞቻቸውም እንዲከበሩላቸው በተደጋጋሚ መጠየቃቸውን የሚናገሩት መምህርቷ ፤ ‹‹አትራፊ ስላልሆናችሁ ደመወዝ አይጨምርላችሁም›› የሚል መልስ ከሸማቾች እንደተሰጣቸው ይናገራሉ።

አቤቱታ አቅራቢዋ እንደሚገልጹት፤ በእርሳቸው ደረጃ በመንግስት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የቤት አበል እስከ 3 ሺብር ፣ የትራንስፖርት (ፐብሊክ ሰርቪስ እና የከተማ አውቶብስ ) እንዲሁም ደመወዛቸው ደግሞ ከ10 ሺህ ብር በላይ ሲሆን፤ የእርሳቸው ግን 30 ዓመታትን በማስተማር አሳለፈው በወር ያልተጣራ 3 ሺህ ብር ብቻ እንደሚከፈላቸው ይናገራሉ። ይህም የኑሮ ውድነቱን ያላገናዘበ ከመሆኑም ባሻገር ሞራልም የሚነካ ድርጊት መሆኑን ያስረዳሉ። «በእኛ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ መንግስት እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ይመልከተው» ሲሉ ቅሬታቸውን ያቀርባሉ።

ሌላኛዋ በደል ተፈጽሞብናል ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን አቤት ያሉት ደግሞ መምህርት አንጓች ታደሰ ናቸው። በአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ከአስራ አምስት አመት በላይ እንደሰሩ ይናገራሉ። እንደ መምህርት አንጓች ገለጻ፤ በትምህርት ቤቱ ለበርካታ አመታት ይስሩ እንጂ የሚከፈላቸው ደመወዝ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና ሌሎች በደረጃቸው ካሉ መምህራን ከሚያገኙት በእጅጉ ያነሰ ነው። በዚህም እኩል እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ መምህር ማግኘት የነበረባቸውን ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ማግኘት አልቻሉም።

በግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ጉዳዩ የሚመለከታቸው በክፍለ ከተማው የሚገኙ አመራሮች ትምህርት ቤቱ እንዲጠገን እና የመምህራንም ጥቅማ ጥቅም እንዲከበር በማለት ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷቸው ነበር። ነገር ግን አንድም ሰው የት ደረሰ? ብሎ ያየ አካል ባለመኖሩ ሁሉም ነገር ባለበት እንዳለ መሆኑን አመላክተዋል።

ከአራት አመት በፊት በትምህርት ቤቱ ልጆቻቸውን የሚያስተምሩ ወላጆች የመምህራን ደመወዝ ያንሳቸዋል በሚል አንድ መቶ ሃምሳ ብር ጭማሪ አድርገው ነበር። ነገር ግን የሸማቾች ቦርድ ለመምህራን አንድም ብር ሳይጨምር ቀረ። ሸማቾች ይህን ሊያደርግ የቻለበት ዋናው ምክንያት መምህራን ትምህርት ቤቱ ተሰላችተው ጥለውት እንዲሄዱ እና መምህራን ትምህርት ቤቱን ጥለው ከሄዱ ‹‹መምህራን የሉም›› በሚል ሰበብ ትምህርት ቤቱን ለሌላ አላማ ለማዋል በማሰብ መሆኑን ያስረዳሉ።

የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ወደ ሸማቾች ከመዞሩ በፊት በአገር አቀፍ ደረጃ በሞዴልነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ነበር የሚሉት መምህርቷ፤ በዚህም ከትምህርት ቤታቸው ተሞክሮ ለመውሰድ ከመላው አገሪቱ የሚገኙ መምህራን ወደ ትምህርት ቤታቸው ይመጡ እንደነበር ያስታውሳሉ። አሁን ላይ ግን ‹‹ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ›› እንዲሉ በሞዴልነት ተመርጦ ለጉብኝት ሊበቃ ይቅርና የትምህርት ቤቱ እድሳት ተደርጎለት ስለማያውቅ ተማሪዎች በጎርፍ ውስጥ ሆነው ለመማር መገደዳቸውን ይናገራሉ።

ስለሆነም የትምህርት ስራው ጨርሶ ሳይጠፋ ትምህርት ቤቱ ወደ መንግስት መዞር እንዳለበት ያመላክታሉ።

### የወላጅ ፣ መምህራን እና ተማሪዎች ህብረት ኮሚቴ ሰብሳቢ ምላሽ

አቶ ወንድወሰን ፍታሌ በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 የወላጅ ፣መምህራንና ተማሪዎች ህብረት ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። እንደ አቶ ወንድወሰን ገለፃ፤ በህጻን ዓለም የተፈጠረው ችግር ከዘጠኝ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ነው። ጉዳዩ ለበርካታ ዓመታት ሰሚ ጆሮ ባለማግኘቱ ችግሩ እየተባባሰ መጥቶ አሁን ላይ ወላጆችን፣ ተማሪዎችን እና መምህራን ክፉኛ እያስለቀሰ ይገኛል።

ማንኛውም ሰው፣ ማንኛውም ኮሚቴ፣ ማንኛውም አካል የተሰጠውን ስራ በአግባቡ ካልሰራ በህግ ሊጠየቅ እንደሚችል በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ እና የፍታብሄር ህግ ተደንግጓል። አንድ ሰው ወይም አካል በኃላፊነት በተሰጠው ስራ ላይ አፈጻጸሙ ችግር ካለበት፤ የአቅም ማነስ ከታየበት ፤ የተሰጠውን ኃላፊነት ለሰጠው አካል የማስረከብ ግዴታ አለበት።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

ይህንን አለማድረግ አይቻለም ይላሉ።

ነገር ግን በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የሚገኘው የሸማቾች ህብረት የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣት አልችል ብሎ በግልጽ እየታየ ለምን ብሎ የሚጠይቀው አካል ስለሌለ ብቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሰራ ያለው ተግባር አገርን እና ሕዝብን በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳ እንደሚገኝ ያስረዳሉ።

በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሸማቾች ስር እንዲተዳደሩ የሚያስገድድ አሰራርም ሆነ የህግ አግባብ የለም። ነገር ግን በ2004 ዓ.ም የነበሩ የክፍለ ከተማ እና ወረዳ አመራሮች በማን አለብኝነት ትምህርት ቤቱን ለሸቀጥ ነጋዴ አሳልፈው ሰጡ። እዚህ ላይ በደንብ ማስተዋል የሚገባው በሕዝብ እና በመንግስት ስም የሚሰሩ ብዙ ችግሮች አሉ። እነኚህን ችግሮች እስከመጨረሻው መታገል ያስፈልጋል።

‹‹እኔ የሸማችም አባል ነኝ፤ የወረዳው የወተመህ ሰብሳቢ ነኝ። ሸማች መስራት ያለበትን ለይቶ ከተማ አስተዳደሩ ሊሰጠው ይገባል። የትምህርት ጉዳይ ደግሞ በትምህርት ባለሙያ በአግባቡ ሊመራ ያስፈልጋል። አሁን ሰዎች እየተጎዱ ነው፤ ትውልድ እያጣን ነው። የትምህርቱ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል።›› ስለዚህ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

መንግስት ያወጣው ፖሊሲ እንደሚያመላክተው አንድም ህጻን እቤቱ መቅረት የለበትም የሚል ነው። ነገር ግን በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 እየሆነ ያለው የእዚህ ተቃራኒ ነው። ወደ ትምህርት ቤት የሄደን ህጻን ትምህርት ቤቱን ነጥቀው ወደ መጠጥ ቤት ቀይረውታል። በዚህም በወረዳው የሚገኙ ህጻናት በአቅራቢያቸው በሚገኝ ትምህርት ቤት ተዝናንተው መማር ሲገባቸው በአንድ ትምህርት ቤት ታጭቀው እና ተጨናንቀው ለመማር ተፈርዶባቸዋል ይላሉ።

ይህን ጉዳይ በሌላ ሚዲያ ለሌላ አካልም በዝርዝር ለማስረዳት መሞከራቸውን ጠቅሰው፤ ነገር ግን ለችግሩ መፍትሄ የሚሰጥ እንደጠፋ እና አሁንም ድረስ እንዳልተፈታ ያስረዳሉ። ለእዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት ምን አልባትም ችግሩን የፈጠሩት ሰዎች አሁንም በተሃድሶ ሰበብ ስልጣን ላይ በመገኘታቸው ነው ይላሉ። ይህም አሁን ላይ ችግሩን ከባድ አድርጎታል። ሆኖም ጉዳዩ እልባት ሳይገኝለት እንደማይቀር ያመለክታሉ።

በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት መምህራን ከ14 እስከ 30 እና ከዚያ በላይ ዓመት ያገለገሉ ናቸው። ሆኖም የሚያገኙት ደመወዝ እጅግን ዝቅተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኑሮን በአግባቡ ለመግፋት የሚያስችል አቅም አጥተዋል። መምህራን በኑሮ ከመጉዳቱም ባለፈ አንድ አይነት ስራ ከሚሰሩ ሌሎች መምህራን ጋር በእኩል አለመታየታቸው ከፍተኛ የሞራል ስብራት እንዲያጋጥማቸው አድርጓል ይላሉ።

በተለይ ሁለቱን ትምህርት ቤቶች በአደራ እያስተዳደረ የሚገኘው የወረዳ 6 የሸማቾች ማህበር ለመምህራኑ ተገቢውን ክብር መስጠት ባይችል እንኳን ትውልድ የሚቀርጹ መምህራንን ክብር ሊነካ እንደማይገባው አሳስበዋል። የሸማቾች ማህበሩ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ለምን ብለው የሚጠይቁ መምህራንን ‹‹ነገ ትባረራላችሁ›› የሚል ዛቻና ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል። ትውልድ ይቀርጻሉ ተብሎ ኃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት በዚህ መልኩ ማስተናገድ ህግን የጣሰ መሆኑን አቶ ወንደወሰን ያስረዳሉ።

‹‹ልጆቻችንን በቅንነትና በታማኝነት ተረክበው በማስተማር ጊዜያቸውን እየገፉ ያሉ መምህራን ሊመሰገኑ ሲጋባቸው በዚህ መልኩ እየተገፉ ሊሰቃዩ አይጋባም። መንግስት የጉዳዩን አንገብጋቢነት ተመልክቶ በአፋጣኝ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል›› ይላሉ።

## የወረዳ 6 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ምላሽ

አቶ አበራ አብጊና በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ናቸው። ከላይ በተነሳው የመምህራን ቅሬታ ዙሪያ በሰጡት ምላሽ፤ በወረዳው ያለው የአጸደ ህጻናት ፍላጎት እና ያለው ተደራሽነት አይመጣጠንም። ይህንንም ተከትሎ በፈረቃ ለማስተማር የተገደዱባቸው ጊዜያት ነበሩ። የትምህርት ቤት እጥረቱን ለመፍታት መንግስት ተጨማሪ አጸደ



አቶ ወንድወሰን ፍታሴ



አቶ አበራ አብጊና

ህጻናት አስገንብቷል። ከዚህ በተጨማሪ በወረዳው የነበረውን የትምህርት ቤት እጥረት ለማቃለል የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት የነበሩበትን ክፍተቶች በመሙላት ሲሰሩ ቆይቷል።

የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት እምቅ ሃብት ያለው ትምህርት ቤት ነው። ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ያለውን ሃብት ለመጠቀም የሚያስችል አመራር የለውም። ይህን ተከትሎ ትምህርት ቤቱን ከሚያስተዳድረው ሸማቾች ቦርድ ጋር በመነጋገር ትምህርት ቤቱ ወደ መንግስት ስለሚዞርበት ሁኔታ ለበርካታ ጊዜያት መወያየታቸውን ያስታውሳሉ።

‹‹ህጻን ዓለም የሚባለው ትምህርት ቤት ወደ መጠጥ ቤት ተቀይሯል። የተቀየረበት አግባብ ስህተት ነው። በዚህም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ከሸማቾች ጋር በነበራቸው ውይይት ትምህርት ቤቱ ወደ መጠጥ ቤት መቀየሩ ስህተት መሆኑን መተማመን ላይ ተደርሷል። በዚህም ትምህርት ቤቱ እስከ ሰኔ 30/ 2014 ዓ.ም ድረስ ወደ ትምህርት ቤት እንዲቀየር አቅጣጫ ተስጥቷል። ይህ አቅጣጫ የሰጡት የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት እና የክፍለ ከተማው ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም ባህል እና ቱሪዝም በጋራ በመሆን ነበር። ስለዚህ ትምህርት ቤቱን ለመቀበል ሰኔ 30ን እየጠበቅን ነው›› ይላሉ።

ኃላፊውም በበኩላቸው ትምህርት ቤቶቹ ተገቢ ተልዕኳቸውን መፈጸም እንዲችሉ በማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት አሁን ላይ ሁሉም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት እርስ በእርሳቸው ሊደጋገፉ ይገባል። አለበለዚያ በታሪክ ተወቃሽ እንሆናለን ሲሉ ይገልጻሉ።

የህጻን ዓለም እና የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት መምህራን ከዲፕሎማ እስከ ዲግሪ የሚደርስ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው እና ለበርካታ አመታት በመምህርነት ያገለገሉ ናቸው። ይሁን እንጂ ተጣርቶ በእጃቸው የሚደርሳቸው ደመወዝ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ እስከ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ነው። ይህ ደግሞ ልክ እንዳልሆነ ትምህርት ጽህፈት ቤቱ ባደረገው የዳሰሳ ጥናቱ አረጋግጧል። የኑሮ ውድነቱን እና የመምህራን ደረጃ ያላገናዘበ ደመወዝ የመምህራንን ስነ ልቦና ከመጉዳቱ ባሻገር እንደ አገር ለመምህራን የሚሰጠውን ክብር የሚነፍግ እና በትምህርት ጥራት ላይም የራሱ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ አስነዋሪ ተግባር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ላይ እየተደረገ ያለው ያልተገባ ስራ በአፋጣኝ እንዲቆም ለማድረግ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት መጠየቃቸውን የሚናገሩት ኃላፊው፤ በክፍለ ከተማ እና በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የፖለቲካ አመራሮች ጣልቃ ገብተው አስተዳደራዊ መፍትሄ ይሰጡታል የሚል እምነት እንዳላቸው ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ፋና አጸደ ህጻናት የሚባል ትምህርት ቤት በአመራር ችግር መዘጋቱን እና የህጻን ዓለም ትምህርት ቤት ደግሞ የደረሰበት የሚታወቅ ነው ያሉት ኃላፊው ፤ ከዚህ ቀደም በአገር አቀፍ ደረጃ በሞዴልነት ይጠቀስ የነበረው አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት አሁን ላይ የትምህርት ጥራት ተቆጣጣሪ ሊዘጋው ጫፍ ደርሷል ሲሉ ይገልጻሉ። ስለሆነም አስቸኳይ መፍትሄ እንደሚያሻው ጠቁመው፤ ይህ ካልሆነ ግን ትምህርት ቤቶቹ እስከመዘጋት የሚያደርስ ለከፋ ችግር ሊጋለጡ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል።

‹‹ለመምህራን የሚከፈለው ደመወዝ መስተካከል አለበት። ልክ አይደለም። በእነኚህ ትምህርት ቤቶች የሚያስተማሩ መምህራን ኢትዮጵያዊ ዜጎች ናቸው። የሸማቾች ማህበር ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር እኩል ደመወዝ እየተከፈላቸው ነው። ሸቀጥ ከሚሸጥ ሰራተኛ ጋር መምህራንን በእኩል ማስተናገድ በትውልድ ላይ ከፉኛ መፍረድ ነው። ምክንያቱም መምህርነት ተተኪ እና አገር ተረካቢ ትውልድን የሚያፈራ ሙያ ያላቸው በመሆናቸው፤ ይህንንም ጉዳይ ወደ ክፍለ ከተማ እና ከተማ አስተዳደሩ ወስደነዋል›› ሲሉ የወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ይናገራሉ።

## በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ምላሽ

ለአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የህብረት ስራ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ለአቶ አብርሃ ታሪክ በእድሳት ምክንያት ከትምህርት ቤት ወደ መጠጥ ቤት ስለዞረው እንዲሁም በአቅም ማነስ ሊዘጋ ጫፍ ስለደረሰው የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት አስመልክቶ ላቀረብነው ጥያቄ በሰጡን ምላሽ፤

የህጻን ዓለም አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ በቅርስነት የተመዘገበ ነው። ቅርስ እንደመሆኑ መጠን ቅርስነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል እድሳት ተደርጎለታል። ከእድሳት በኋላ ግን ቅርሱን በበላይነት የሚያስተዳደረው አካል በቤቱ ትምህርት እንዳይሰጥበት የሚል ደብዳቤ ለሸማቾች ስለላከ ሸማቾችም ቤቱን ሌሎች አማራጭ ስራዎች ለመጠቀም ተገደደ። ስለሆነም ሸማቾች ለሕዝብ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ዘርፎች አንዱ ወደሆነው አማራጭ የሕዝብ መዝናኛነት ቀይሮታል።

አሁን ላይ የአጸደ ህጻናት ትምህርት ቤት የነበረው ቤት የመጠጥ ቤት መሆኑን በምልከታ አረጋግጠናል። ስለዚህ ምን ይላሉ? የሚል ጥያቄ ያነሳንላቸው ሲሆን፤ ቅርሱን በማይጎዳ መንገድ ቤቱን ለመጠጥ ሸያጭ መጠቀም እንደምንችል ቅርሱን በበላይነት የሚያስተዳደረው አካል ፈቅዶልናል ብለዋል።

ነገር ግን የህጻናት የእውቀት መገብያ ቦታ መጠጥ ቤት መሆን ነበረበት ወይስ አልነበረበትም የሚለው ላይ የአሰራር ክፍተት ሊኖር ይችላል ያሉት ኃላፊው፤ የሸማች ማህበሩ ግን ቤቱ ወደ ትምህርት ቤት ቢቀየር እንደሚፈልግ ጠቁመዋል። ይሁን እንጂ ቤቱን ወደ ትምህርት ቤት መቀየር የሚቻለው ቅርሱን በበላይነት የሚያስተዳደረው አካል ሲፈቅድ ብቻ መሆኑን ያስረዳሉ።

አምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት ከዚህ ቀደም በአገር አቀፍ ደረጃ ሞዴል ትምህርት ቤት ተብሎ የተመረጠ እና በአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሳይቀር እውቅና ተሰጥቶት እንደነበር ይታወቃል። ነገር ግን የሸማቾች ቦርድ ትምህርት ቤቱን ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ትምህርት ቤቱ ሞዴል መሆን ይቀርና ጣራው እያፈሰሰ እና ጎርፍ እያስገባ ተማሪዎች መማር እስከማይችሉበት ደረጃ ደርሷል። መምህራንም ተገቢው ጥቅማ ጥቅማጥቅም እያገኙ አልነበረም። በተጨማሪም ሸማቾች የታደሰ ትምህርት ቤት እንኳን ለተገቢው ጥቅም እንዲውል ማድረግ አልቻለም። ይህ ደግሞ ሸማቾች ትምህርት ቤቶችን ማስተዳደር እንዳልቻለ ሁነኛ ማሳያ ነው። ሸማቾች ማስተዳደር ካልቻለ ትምህርት ቤቶችን ለመንግስት የማያስረክበው ለምንድን ነው? ሲል ለቀረበላቸው ጥያቄም እንዲህ ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

‹‹እርግጥ ነው ከዚህ ቀደም የሸማች ማህበሩ ትምህርት ቤቶችን በብቃት ማስተዳደር ላይችል ይችላል። ነገር ከዚህ ቀደም ሲል ማስተዳደር አልቻለም ማለት አሁን ላይ አይችልም ማለት አይደለም። በመሆኑም ትናንት አልቻለም እና አሁን አይችልም ብሎ መደምደም ያስቸግራል›› የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ የአምስት ኪሎ አጸደ ህጻናት የእድሳት ችግር አለበት። ጣራው ያፈሳል፤ ሌሎች እድሳቶች ያስፈልጉታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ትምህርት ቤቱን ከሚያስተዳደረው የሸማቾች ቦርድ ጋር ውይይቶች ተደርጓል። ኮሚቴም ተቋቁሞ የትኛው ጥገና ያስፈልገዋል? የትኛው ምን የጎደለው ነገር አለው? ብሎ ኮሚቴው አጥንቶ የጓደለውን ለማሟላት ስራዎች ተጀምረዋል። የተጓደሉ ነገሮች ተሟልተው በቀጣይ አመት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስራዎች ተጀምረዋል።

መምህራንም የጠየቁትን የሙብት ጥያቄ ለመመለስ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሰራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ተፈጥረው የነበሩትን ችግሮች ለማስተካከል አሁን ላይ ማህበሩ በጥሩ መነሳሳት ላይ ይገኛል። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሰራ ነው ብለዋል።

‹‹የመምህራን ደመወዝ የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው ልክ መከፈል አለበት። ይህ የቢሯችን አሁናዊ አቋም ነው። ከዚህም ባለፈ መስተዳደሩ ለተማሪዎች የፈቀደው ምገባ እና መሟላት ያለባቸው ቁሳቁሶች አሉ። እነኚህን ተማሪዎች እንዲያገኙ እንሰራልን። ነገር ግን በሸማቾች ስር እያሉ ምገባ ማግኘት አይችሉም የሚባል ከሆነ እና ለመምህራንም ማግኘት የነበረባቸው ጥቅማ ጥቅሞች ካልተሟሉ ወዴት መሄድ አለብን? የሚለውን በአጭር ጊዜ እንወስናለን። እኛ ግን ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ለመቅረፍ እንሰራለን›› ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላው የዝግጅት ክፍሉ ያነሳው ጥያቄ ከተወሰኑ ወራት በፊት የወረዳ 6 ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ትምህርት ቤቱን የሚያስተዳደረው የሸማቾች ቦርድ ፣ ወተመህ በተገኙበት በተያዘ ቃለ ጉባኤ ትምህርት ቤቶችን የሚያስተዳደረው አካል ከአቅም ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶችን እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ለወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት ለማስረከብ ተስማምቶ እንደነበር የወረዳው የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ያስረዳሉ። በቃለ ጉባኤ ከተስማማችሁ ለምን እስከዛሬ ትምህርት ቤቱን አላስረከባችሁም ? የሚል ነበር ።

ኃላፊው እንዳስረዱት፤ ስለጉዳዩ በቃል ከመስማት በዘለለ ስለቃለ ጉባኤው የሚያውቁት ነገር የለም። ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቶችን የሸማቾች ቦርድ ማስተዳደር ካልቻለ ትምህርት ጽህፈት ቤት ያነሳው ጥያቄ ተገቢነት ያለው ነው። ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ ቢሻሻል የሚጠቀሙት የሸማች ማህበሩ አባል ልጆች ናቸው። ሸማች ካልቻለ ወደ መንግስት መዞር አለበት። ነገር ግን በምን መልኩ ከተባለ ህጋዊ መስመሩን ተከትሎ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ተማሪዎች ማግኘት የሚገባቸውን እውቀት የማያገኙ ከሆነ ፣ መምህራን ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ማስከበር ካልተቻለ፤ ትምህርት ጽህፈት ቤቱ ይቅርና የሸማቾች ማህበርም ለመንግስት እንዲሰጥ ከማንም በፊት ግንባር ቀደም ሆኖ ይሰራል ሲሉ ተናግረዋል።

በቀጣይ ሳምንት ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር የሚሰጡንን ምላሽ እናቀርባለን።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# "የእንደራሴዎቻችን" የክራሞት ማጠቃለያ

**እንደ ማዋዣ፤**

የኢትዮጵያ ሕዝብ የምርጫ ካርዱን እንደ "ክብር መረማመጃ ቀይ ምንጣፍ በመደልደል" የአገሩን አደራ በጫንቃቸው ላይ አሸክሞ ለፓርላማ ወንበር ያበቃቸው "እንደራሴዎቹ" የሦስት ሩብ ወራት የተግባር ክራሞታቸውን አጠናቀው ከመንበራቸው ወደ "ጓዳቸው" ለመትመም ተሰነባብተዋል። ይህ የምክር ቤቱ የሰኔ 30 የስድስተኛ ዙር፣ የአንደኛ ዓመት የሥራ ዘመን የ16ኛ መደበኛ የማጠቃለያ ስብሰባ ግጥምጥሞሽ አንዳንድ ትዝታዎችን፣ ታሪካዊ እና ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን እንድናስታውስ ግድ ብሎናል። ይህንን ማድረጋችን አንድም ለእውቀት አንድም ለማስታወስ አንድም ለማዋዣነት ይረዳ ስለመሰለን ነው። ውይይታችን ደረቅ በደረቅ እንዳይሆን በመስጋት ጭምር።

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 58 "የምክር ቤቱ ስብሰባና የሥራ ዘመን" በሚለው ዋና ርዕስ፤ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር "የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ሰኔ ሠላሳ ነው፤..." ተብሎ ተደንግጓል። ይህ ዕለት ከሰኔ 30 የትምህርት ቤቶች መዘጋትና አይረሴ የሆኑ የተማሪነት ዘመን የመሰነባበቻ ትዝታዎችን እንድንቀሰቅስ ግድ ይለናል።

የፈተና ውጤታቸው የተሳካላቸው ተማሪዎች በሰኔ ሠላሳ ሲፈነጥዙ፤ በለስ ያልቀናቸው ደግሞ እዬዬ ማለታቸው የተለመደ ነው። ፍንጠዛውና እዬዬው በተማሪዎቹ ተግቶ ማጥናትና ያለማጥናት ስለሚወሰን ለጊዜው በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ለማለት ዐውዱ አይፈቅድልንም። ይህንን ገናና የሰኔ ወርና የመጨረሻውን ቀን የሚያስታውሱ በተማሪዎች የተገጠሙና የሚገጠሙ በርካታ አዝናኝ ግጥሞች ቢታወሱ ባልከፋ ነበር። ከርዕስ ጉዳያችን እንዳያዘናጋን በመስጋት ብቻ እንዘለዋለን።

የፓርላማ ወንበረተኞቻችን የዓመቱ የየግል ቆይታቸው አላባና ገለባ በምን ወንጠፊት ተፈትሾ ማርክ እንደሚሰጣቸው ለጊዜው ዝርዝሩም ሆነ ምሥጢሩ ለወሳኝ ፖለቲከኞች ካልሆነ በስተቀር ለእኛ "ለመራጭ ዜጎች" እንድናውቅ የሚፈለግ ስለማይመስለን "መብታችን ነው" ብለን ለመሟገት አንደፍርም። በግላጭ ቢነገረን ኖሮማ "የምርጫ ካርዳችን ፍሬ ማፍራቱን ወይንም አለማፍራቱን" በሚገባ በገመገምን ነበር።

መቼም ደግ መመኘት በራሱ ደግ ስለሆነ ዲሞክራሲው ሰፋ ቢደረግልን ኖሮማ የመረጥናቸውን "እንደራሴዎቻችንን" ምን ሠራችሁ? ምን ውጤትስ አስመዘገባችሁ? ምን ተግዳሮትስ ገጥሟችሁ ነበር? ብለን በአደባባይና በሚዲያ ፊት በግልጽነት በገመገምናቸው ነበር። ለምን ቢሉ "ለድምጻችን ክብር መስጠቱ ተገቢ ስለሆነ" መልሳችን ይሆናል። ችግሩ የመረጣችሁት "ፓርቲያችንን እንጂ ግለሰቦችን መች ሆኖ" ተብለን በድርጅታዊ አሰራር የሚሰጠውን ምላሽ "የለመድነው ስለሆነ" እጅግም ንትርኩን አናሟሙቅም።

እጅግ የሚያሳዝነው ግን ከመመረጣቸው አስቀድሞ ሜዳው ጠበበን፣ የሕዝብ ብሶትና እምባ እንቅልፍ ነሳን፤ የአካባቢያችንን ችግር በየቀኑ ማስተዋሉ መብል መጠጣችንን አመረረ ወዘተ. እያሉ ሲብከነከኑና ሲያማልሉን የነበሩ "የተከበሩት" የቅርብ ወዳጆቻችንና የሩቅ "ተደናቂዎች" የልባቸው ከሞላላቸው በኋላ ድምጻቸው ከመንበራቸው፤ ወዳጅነታቸው ከወትሮ ስፍራው ጠፍቶ የመሰወራቸው ምክንያት አልገባንም።

እስከ ምርጫው ድረስ እናደርገው እንደነበረ በቡና ላይም ሆነ በአጋጣሚ ስንገናኝ በእለት ተእለት ውሎ አምሽቷችን "አገር እንዴት ሰነበተች?" እየተባባልን ልንወያይ ቀርቶ የስልክ ግንኙነቱ ራሱ የተቋረጠው "የአፈ ጉባኤው መዶሻ" ጠረጴዛው ላይ ባረፈ የመጀመሪያው ቀን ነበር።

"የእናንተን የመራጮቼን ጥያቄ የተፈለገውን ዋጋ ከፍዬም ቢሆን አስፈጽማለሁ" ተብሎ የተገባልን ቃል ኪዳንም "ከተወካዮቻችን ዘንድ" እንደ ማለዳ ጤዛ በንኖ የተዘነጋ መስሎን በትዝብት አልፈነዋል። ዳሩ ከእነርሱ አእምሮ ይጠፋ ይሆናል እንጂ ከእኛ "ከምስኪን መራጮች" ልብ ግን ትዝብቱ ሊዘነጋ አይችልም። "ተራ ሰው" የመሆናቸው ቀን መድረሱ ስለማይቀር የምርጫ ዘመናቸውን አጠናቀው ሲቀላቀሉን "ትዝብቱ ለሚተርፋቸው ለእነርሱ ይብላኝላቸው" ከማለት ውጭ እኛ መራጮችማ ምን ማለት እንችላለን?

ሌላው የሰኔ ወር የመጨረሻ ቀናት በአብዛኞቹ የአገራችን አካባቢዎች ለገበሬው ልዩ ትርጉም ያላቸው መሆናቸው የሚታወቅ ነው። ገበሬው በሬውን ጠምዶ "ሆ!" እያለ በሙሉ ኃይሉ ወደ መኸር እርሻው የሚገባው በእነዚሁ የሰኔ መጨረሻ ቀናት ነው። "አንድ ሰኔ ያቆሰለውን ዘጠኝ ሰኔ አይፈውሰውም" የሚባለውም አርሶ አደሩን ለሥራ ለማበረታታት ታስቦ ነው። "ሰኔ ሲመጣ ድግር ቆረጣ" እንደማይቻልም ሥነ ቃሉ ይመክራል።

የታታሪውን ገበሬ የክረምት ውሎ ማስታወሳችን አለብልሃት አይደለም። የአገራችን የእንደራሴዎች ምክር ቤት በሰኔ ሠላሳ እንዲዘጋ የተወሰነበትን ተለምዷዊ ዳራ ከክረምቱ ተፈጥሯዊ ባህርይ ጋር እያስተያየን አንዳንድ ሃሳቦችን እንሰንዝር። መንገድንና ድልድዮችን የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ባልተስፋፉባት የትናንቷ ኢትዮጵያ በሐምሌና በነሐሴ ወራት ወንዞች ስለሚሞሉ ከግብርና በስተቀር ብዙ ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎች ይገደቡ ነበር። ስለዚህም ሁለቱ ወራት መሰባሰቢያ እንጂ እንደ ልብ ከቦታ ቦታ የሚጓጓዙባቸው አልነበሩም።

ሕገ መንግሥታችን ለዚህን መሰሉ "የትናንት እውነታ" እስረኛ ለመሆን ፈልጎ ይሆን ወይንም ሌላ ምክንያት ይኑረው ባይታወቅም፤ የሕዝብ እንደራሴዎቹ "ክረምቱ ጫን ሳይልና ወንዞች ሳይሞሉ ወደየመጡበት የምርጫ ክልል በጊዜ እንዲሰበሰቡ አዝኖላቸው" የሚሸኛቸው ጥንት ከተለመደው "ባህል" መላቀቅ ቢሳነው ይሆንን ብለን መጠየቃችን አልቀረም። ከሆነ መቼስ ምን እንላለን። "ልማድ ከጅማት እንደሚበረታ" የታወቀ ስለሆነ የዘመናዊ መጓጓዣዎች መኖር ተዘንግቶ ስለሚሆን "ለምን?" ብለን አንሞግትም።

ምክንያቱ በርግጥም "እንደራሴዎቻችንን ከወንዞች ሙላት ለመታደግ ታስቦ ከሆነ" ተመልሰው ሲሰባሰቡ የአገሪቱ ሁነኛ በጀት በመንገድና በድልድይ ግንባታዎች ላይ እንዲውል አጥብቀው ሊሟገቱ ይገባል። ቢሆንልንማ ኖሮ የሚሻለው "ተወካዮቹ" በተፋፋመው የበጋ ወራት አርፈው ትምህርት ቤቶች በሚዘጉበት ወራት ሥራቸውን ቢከውኑ ኖሮ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረው ነበር ብለን እናምናለን። እንዴታውን እናብራራ።

የፓርላማው ዓመታዊ የእረፍት ዝግ በበጋ ወራት ቢሆንና ዋነኛው ሥራቸው የነገይቱ ኢትዮጵያ ተረካቢ ወጣቶች ከትምህርት ገበታቸው ላይ በሚያርፉባቸው የክረምት ወራት ቢሆን መልካም ነበር። ልጆቻችን በክረምት ወራት በእረፍት ላይ ስለሚሆኑ የምክር ቤቱን ውሎና አዳር ሃሳባቸውን ሰብስበው በሚገባ ለመከታተል እድል ያገኛሉ። ስለ መንግሥታዊ አሠራሮችም ለመወያየትና ለመተቸት በእጅጉ ይመች ነበር።

ገፋ ካደረግነውም በየእርከኑ ባሉት የየአካባቢዎቻቸው መሰል የተወካዮች ስብሰባ (ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ) በታዛቢነት እየተገኙ "በነጋቸው" ላይ የሚሰጡ ሃሳቦችንና ውሳኔዎችን ቢከታተሉ፤ ከታዘነላቸውም "ተወካዮቻችን" ብለው "የመረጧቸውን እንደራሴዎቻቸውን" የሚሞግቱባቸው እድሎች ቢመቻቹላቸው ብዙ ጠቀሜታ ሳይኖረው አይቀርም የሚል ግምት አለን። በሌሎች አገራት ይህን መሰል "ባህል" የተለመደ መሆኑን ልብ ይሏል።

በተለየ ሁኔታ ግን እንደ በቀደም እለቱ በሚሊዮን ቁጥሮች የሚታወቁት ተማሪዎቻችን የዓመቱ የእንደራሴዎች የማጠቃለያ ስብሰባ በሚደረግበት እለት በወሳኝ የመጨረሻ ፈተና ላይ ስለሚሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩንና የወንበረተኞችን ውይይት ልብ ተቀልብ ሆነው ስለመከታተላቸው እርግጠኛ ለመሆን ያዳግታል።

ሕገ መንግሥቱ ክረምቱን ለእንደራሴዎች እረፍት የወሰነው "የመረጣቸውን ሰፊውን አርሶ አደር አግኝተው እንዲያወያዩ ታስቦ ነው" የሚል ምክንያት የሚቀርብ ከሆነም "ከገበሬው የግብርና ስራ ውጥረት ጋር እቅዱ አብሮ ይጎዳኛል ወይ?" ብሎ ሊያስጠይቅ ይችላል። ምክንያቱ ይህ ከሆነም እንደራሴዎቹ ከእረፍት ሲመለሱ ሪፖርታቸው ላይ ጫን ብለው ስለየአካባቢያቸው አርሶ አደሮች ስኬትና ጉድለት በሚገባ እንደሚወያዩበት ተስፋ እናደርጋለን።

**የሰኔ ሠላሳ የእንደራሴዎቻችን ውሎና ትዝብታችን፤**

የበቀደሙን የፓርላማ ውሎ ብዙው ሕዝብ የተከታተለው በልዩ ንቃት ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው። ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይቀርባሉ ተብለው የተገመቱ በርካታ አገራዊ ጉዳዮች በሕዝብ አንደበት ሲጉላሉ መክረማቸው ነው። "ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህና በዚያ ጉዳይ ላይ ምን መልስና አስተያየት ይሰጡ ይሆን?" የሚለው የሕዝቡ ጉጉት የማጠቃለያ ስብሰባው በጉጉት እንዲጠበቅ ምክንያት ሆኗል።

በትልቅ ጉጉት ሲጠበቁ የነበሩት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ያለወትሯቸው ፈገግታቸውን ደብዘዝ አድርገው መታየታቸው በአብዛኞቹ ዜጎች ላይ ግራ የመጋባት ስሜት ሸው ብሎባቸው እንደነበር ብዙዎች ሲናገሩ ተደምጠዋል። ለመሪ ከሚሰጠው የአክብሮትና የመወደድ መገለጫዎች አንዱ አካላዊ ገጽታ እንደሆነ የሰለጠንበትና ለማሰልጠን ዕድል ያገኘንበት የኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ (Nonverbal communication) ፍንጩን ይሰጠናል። ለማንኛውም ውይይቱ እየተሟሟቀ ሲሄድ ስሜታቸውም ፈታ ማለቱን ወደነዋል።

ከአሁን ቀደም የፓርላማውን ውሎ በተመለከተ ትዝብታችንን የገለጽንባቸውን አንዳንድ ጉዳዮች መለስ ብሎ ማስታወሱ ተገቢ ይመስለናል። በመሠረቱ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚቀርቡት ጥያቄዎች አጭርና ግልጽ መሆን ይገባቸዋል የሚል እምነት አለን። ምክንያቱም የፓርላማውን ሰዓት መሻማቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ወንበረተኛ ያልሆኑ በርካታ ታዛቢ የአገር ውስጥና የውጭ ዜጎች እንዳሉ ልብ ማለቱ ግድ ይላል። በሌላ አንጻርም አንድ ጥያቄ ለማቅረብ ዙሪያ ጥምጥም መዞሩ በፍጹም ተገቢ ነው የሚል እምነት የለንም።

አንድን ጥያቄ ለመጠየቅ ወደ ኋለኞቹ ዘመናት ተንደርድሮ ታሪክ መተረክ፣ ነገሮችን ለጥጦ ማብራራቱ ለጊዜው መድረኩ ስለማይፈቅድ ቁጥብነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል። ለምሳሌ፡- "የኢትዮጵያና የሱዳን ወቅታዊ ግንኙነት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? እንዲህና እንዲህ የሚል መረጃ ስላለን ጉዳዩን ቢያብራሩልን?" ብሎ መጠየቅ እየተቻለ አንድ እንደራሴ ያንን ሁሉ ታሪካዊ ዳሰሳ ለማድረግ ለምን እንደፈለጉ አልገባንም። ከዚህ በተቃራኒው አንዳንድ ጠያቂዎች ቅልብጭ ያለ ጥያቄ መጠየቃቸው የሚያስመሰግናቸው ስለሆነ ሊበረታቱ ይገባል።

ይህ ጸሐፊ ከአሁን ቀደም እንደገለጸው ቢያንስ በዚህ የተከበረ ፓርላማ ውስጥ እድል አግኝተው ወንበር የያዙ እንደራሴዎች ሊከራከሩና ሊሟገቱ የሚገባቸው በፌዴራል ደረጃ በተሰሩና በሚሰሩ አገራዊ ፕሮጀክቶች ላይ እንጂ ለመጡበት የወረዳ ወይንም የዞን አለያም የክልል ምክር ቤቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎች መጠየቃቸው አግባብ ይሆንን ? ለምሳሌ፡- የልማት ፕሮጀክቱ የፌዴራሉ ድርሻ መሆኑን እንኳን ሳይገልጹልን "ያ መንገድ፣ ያኛው ድልድይ፣ ያኛው ምንትስ" እያሉ ፓርላማውና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊመለከቷቸው ሥልጣን ባልተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ጊዜ ማባከኑ ለጊዜው ይህንን ጸሐፊና መሰል "መራጭ ዜጎችን" ግራ ማጋባቱ አልቀረም።

አንድ የፓርላማ ወንበረተኛ አንድን ጉዳይ ለክርክር ወይንም ለግልጽነት ጥያቄ ወይንም አስተያየት ሲያቀርብ በቂ ጥናትና አጥጋቢ መረጃ ሰብስቦ መሆን አለበት እንጂ ለመጠየቅ ብቻ የሚጠየቁ የሚመስሉ ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄ ቢደረግና ተደጋግመው የሚሰነዘሩ ጥያቄዎችን በተመለከተም ለወደፊቱ ቢታሰብበት አይከፋም።

"ጥያቄዬን በንባብ አቀርባለሁ"፣ "ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ጥያቄያችንን ለመመለስ በመሃላችን ስለተገኙ እናመሰግናለን" የሚሉ መሰል ተደጋጋሚ (ያውም ጥያቄ ለማቅረብ እድል ባገኙት ተወካዮች ሁሉ) የንግግር መቅድም አቤቱታዎች ጉዳይ ደጋግሞ ቢመከርበት ይበጅ ይመስለናል።

ቢቻል እንደራሴዎቹ ጥያቄያቸውን በቃል አሳጥረው ቢያቀርቡ፤ ካልሆነም በየትኛውም የአገራችን ቋንቋ ሊሆን ይችላል በአግባቡ ቢያነቡልን መልእክቱ ለእኛ ለተመራጭ ዜጎች ያለምንም መንገራገጭ ሊደርሰን ይችላል። የጠቅላይ ሚኒስትሩን መገኘት በተመለከተም በእንደራሴዎቹና በራሳቸው ስም አፈጉባኤው የመግቢያ ንግግራቸው ውስጥ አንዴ ካመሰገኑ በቂ ይመስለናል።

በተረፈ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን "ይህንን ሕግ ያጸደቀው ይህ ፓርላማ አይደለም!" የሚለው አስተያየት ለብዙ ዜጎች ግርታ እንደፈጠረ መሸሸጉ አስፈላጊ አይመስለንም። በየትኛውም የፓርላማ ዘመን የጸደቀ ሕግ እስካልተሻረ ድረስ ማን፣ መቼና እንዴት አጸደቀው ተብሎ የሚጠየቀው ለእውቀትና ለምርምር እንጂ የገዢነቱ ክብርማ እንደተጠበቀ መቆየቱ የታወቀ ነው።

በመጨረሻም የመረጥናቸው እንደራሴዎች ተገዢነታቸው "ለሕገ መንግሥቱ፣ ለሕዝቡና ለሕሊናቸው" እንደሆነ በግልጽ ስለተደነገገ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ በረከቶች ከወንበረተኞቹ መንበር እንዲፈልቁ የሚያንጹ አስተያየቶችን መስጠቱ ተገቢ ስለሆነ ይህንን ብለናል፤ ወደፊትም መባል የሚገባውን ቅድሚያ እየሰጠን ብዕራችንን እናተጋለን። ሰላም ይሁን !

# የግብርና ምርቶች «ብራንድ» - ለአምራችና ሸማቹ ተጠቃሚነት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



የግብርና ምርቶችን በብዛትና በጥራት በማምረት ለኢንዱስትሪ፣ ለኤክስፖርት፣ ከውጭ አገር የሚገባን ምርት በአገር ውስጥ ለመተካት እና የአገር ውስጥ የዜጎች የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት እንዲቻል ሰፊ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል። የአገሪቱ የግብርና ምርቶች ደረጃቸውን የጠበቁና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ይሁንና ምርቶቹን ለገበያ በማቅረብ ሂደት በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ። በተለይም እሴት የማይጨምሩ በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ በርካታ ደላሎች የንግድ ስርዓቱን ገበያውን ሲረብሹት ይስተዋላል። በዚህ ጤናማ ባልሆነ የንግድ ሂደት አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጠቃሚ እየሆኑ አይደሉም።

ምርትና ምርታማነት የቱንም ያህል ቢያድግ የግብይት ስርዓቱ ዘመናዊነት በተላበሰና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ካልተመራ የአምራችና የሸማቹን ፍላጎት ማሟላት አይቻልም። አምራቹ የምርቱ ተጠቃሚ መሆን ካልቻለ ሌላ ምርት ለማምረት ይነሳሳል፤ ይህን ተከትሎ ተጠቃሚውም ይጎዳል።

ይህን ችግር መነሻ በማድረግም በቅርቡ በኢትዮጵያ ኅብራት ሥራ ኮሚሽን አነሳሽነት በአይነታቸው የተለዩ በኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የሚመረቱ የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንች እና የጨንቻ አፕል ምርቶች አዳዲስ የብራንድ መለያዎች እንዲወጣላቸው ተደርጓል፤ ብራንዶቹን የማስተዋወቅ ተግባር ከሰሞኑ ተከናውኗል።

ምርቶቹ ዕውቅና በተሰጣቸው ወቅትም የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ አያልሰው ወርቅነህ እንደገለጹት፤ የእነዚህ የግብርና ምርቶች ዋና ዋና ፈተናዎች ከሆኑት መካከል በአገር አቀፍ ገበያ በስፋት ተደራሽ መሆን አለመቻል፣ ደካማ የግብይት ትስስር፣ የገበያ መሰረተ ልማት እጦት እና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ጥቂት ነጋዴዎችና ደላሎች እንዳሻቸው የዋጋ ተመን በማውጣት ገበያውን እየተቆጣጠሩ ግብይቱን እያዛቡና እየገደቡ ያሉባቸው ሁኔታዎች ይጠቀሳሉ። በዚህ የተነሳም አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጠቃሚ መሆን እየቻሉ አይደለም።

ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ከግብርና ሚኒስቴር እና ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ምርቶቹ በሚገኙባቸው ክልሎች ያሉ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር፣ ምርታማነትን ማሳደግና የምርቶቹን የግብይት ስርዓት ማዘመን እንዲቻል የተመረጡ የሙዝ፣ የአፕልና የድንች ምርቶችን ብራንድ በማድረግ ከተዛባ የገበያ ስርዓት የሚወጡበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየሠራ ይገኛል።

«የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንችና የጨንቻ አፕል ምርቶች አዳዲስ የብራንድ እሴቶችና መለያዎች ምርቶቹ ሰፊ የገበያ መዳረሻዎች እንዲኖራቸው ያደርጋል» ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በተለይም የአርባ ምንጭ ሙዝ በተለየ ሁኔታ በሂደት በዓለም አቀፍ ገበያ ጭምር እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲሉ አስታውቀዋል። ይህም የአምራቹን ኑሮ በማሻሻል የጎላ አገራዊ ፋይዳ እንደሚኖረው አስረድተዋል።

የአማራ ክልል ህብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ወልደትንሳኤ መኮንን እንዳሉት፤ በክልሉ 23ሺ259 የህብረት ሥራ ማህበራትና 72 ዩኒየኖች ይገኛሉ። እነዚህ የህብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ለገበያ ያቀርባሉ።

በአስር ዓመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድ አስር የግብርና ምርቶች ብራንድ ይደረጋሉ ተብሎ ዕቅድ ተይዟል ያሉት አቶ ወልደትንሳኤ፣ ከአስሩ መካከልም ሶስቱ ብራንድ መደረጋቸው በሶስት ምክንያቶች ወሳኝና እንደሆነም አንስተዋል። አንደኛው ገበያው ውስጥ በመለያው ለመድረስ፤ ሁለተኛው ምርቱ ተሻሽሎ በስፋት እንዲመረት ለማስቻል፤ ሶስተኛው ደግሞ ምርቱ በመሀል የገበያውን ስርዓት የሚያበላሹትን አልፎ በብራንዱ ወይም በመለያው መሰረት ወደ ገበያ እንዲገባ በማስቻልና ተጠቃሚውን ተደራሽ ማድረግ ይቻላል ሲሉ ያብራራሉ።

እነዚህ ምርቶች ወደ ገበያው የሚገቡትም በተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሲሆን፤ ለአብነትም የአዊ ብሔረሰብ አስተዳዳር ዞን የዘንገና አትክልትና ፍራፍሬ ኅብረት ሥራ ዩኒየን አዲስ አበባ ገበያ ድረስ ይዞ ይገባል። ብራንድ ሆኖ ወደ ገበያው ሲገባም በዋጋም ሆነ በመጠን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለመሆን የተሻለ አማራጭ ይፈጥራል።

**የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንችና የጨንቻ አፕል ምርቶች አዳዲስ የብራንድ እሴቶችና መለያዎች ተዘጋጅቶላቸዋል፤ ይህ መሆኑም ምርቶቹ ሰፊ የገበያ መዳረሻዎች እንዲኖራቸው ያደርጋል። ሁኔታው በተለይም የአርባ ምንጭ ሙዝ በተለየ ሁኔታ በሂደት በዓለም አቀፍ ገበያ ጭምር እንዲቀርብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ይህም የአምራቹን ኑሮ በማሻሻል እንዲሁም የጎላ አገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል**

ገበያው ውስጥ ጥሩ ግብይት እንዳይኖር ከሚያደርጉ ችግሮች መካከል አንደኛው የምርት መጠን ማነስ ሲሆን፤ ሁለተኛው በአምራቹና በሸማቹ መካከል ያለው የግብይት ሥርዓት ነው። ሌላው ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶችን ከማቅረብ አንጻር የሚታዩ ችግሮችና በአምራቹና በሸማቹ መካከል ያለው የዋጋ ሁኔታ ስርዐት አልበኝነት ያለበት መሆኑ ነው።

አቶ ወልደትንሳኤ እንዳሉት፤ ይህን ብልሹ የገበያ ሂደት ለማስተካከልም ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። አምራቾች ተደራጅተው ምርቱን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ያስገባሉ። ኅብረት ሥራ ማህበራቱም ምርቱን ወደ ገበያ በማስገባት ለተጠቃሚው ተደራሽ ያደርጋሉ። በዚህ መሰረት ገበያውን ስርዓት ማስያዝ ይቻላል። አጠቃላይ የገበያ ሥርዓቱን ጤናማ ማድረግ እንዲቻልም ምርቶችን ብራንድ የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ከመቼውም ጊዜ በተለየ በአሁኑ ወቅት የኅብረት ሥራ ማህበራት ራሳቸውን እያደራጁ ጥሩ ድጋፍ እያረጉ መሆኑን ጠቅሰው፣ በፋይናንስ ረገድም መንግሥት እየደገፈ መሆኑን ነው ያመለከቱት። በተለያዩ አደረጃጀቶች ስልጠናዎችን በማዘጋጀት መንግሥት እየደገፈ ነው። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም የተሻሻለ ምርጥ ዘር እያቀረበ ይገኛል። ከዚህ አንጻር ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲጠናከሩ በራሳቸው ምርጥ ዘር እንዲያመርቱና ተደራጅተው ገበያ ውስጥ እንዲገቡ እየተደረገ ያለው ሥራ አበረታችና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ተግባር ነው ሲሉ ያብራራሉ።

«መደራጀት አንድነት ነው» በማለት በህብረት ሥራ ከተደራጁ ጊዜ ጀምሮ ሀሳባቸው መደመጥ እንደቻለና ምርትና ምርታማነት ላይም ውጤት ማስመዝገብ እንደቻሉ የገለጹት አርሶአደር ምክሩ ታረቀኝ በአማራ ክልል አዊ ዞን ዳንግላ ወረዳ የዘንገና መስኖ ቦርድ ሰብሳቢ ናቸው።

እንደ አርሶ አደር ምክሩ ገለጻ፤ አርሶ አደሮች በኅብረት ሥራ አማካኝነት የተለያዩ ዘሮችን ለአባሎቻቸው በቀላሉ ማግኘት ችለዋል። ምርቶቹንም ብራንድ ማድረግ ወይም መለየት መቻሉ በገበያ ይበልጥ ጠቃሚ መሆን ያስችላል። በገበያ ትስስር ምንም እሴት ከማይጨምሩ ደላላና ነጋዴዎች አርሶአደሩን ለመታደግ ይጠቅማል።

በአሁኑ ወቅት የአካባቢው የድንች ምርት ብራንድ መደረጉና መተዋወቁ ጤናማ የገበያ ስርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል ሲሉም አርሶ አደሩ ተናግረው፣ ምርቱም ማህበራቱ በተደራጁበት አግባብ ለዩኒየኑ በቀጥታ ያደርሳል፤ ዩኒየኑም በቀጥታ ለሸማቹ ያቀርባል ብለዋል። በዚህም በቅድሚያ አባላቱ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፣ ሸማቹም ያለደላላ ምርቱን ማግኘት በመቻሉ ተጠቃሚ ይሆናል ይላሉ።

አርሶ አደር ምክሩ አርሶ አደሩ ሰፊ የገበያ ትስስር የፈጠረ እንዳልሆነና በዚህም ምክንያት በስፋት ወደ ማምረቱ ስራ እንዳልገባም ይጠቅሳሉ። ትስስሩ ቢኖር ምርቱን አሁን ከሚያመርተው በእጥፍ ማምረት እንደሚቻልም ነው የሚጠቁሙት። በሙሉ አቅም ለማምረት የገበያ ትስስሩ አለመኖር እንደጎዳቸው ይገልጻሉ። ሌሎች ምርቶችም እንዲሁ የገበያ ትስስር የተፈጠረ ባለመሆኑ በስፋት ወደ ማምረቱ መግባት እንዳልተቻለም ጠቅሰው፣ በአሁኑ ወቅት እንዲህ አይነት የገበያ ትስስር በመፍጠር ምርቶቹን ብራንድ ማድረግ ወይም ማስተዋወቅ መቻሉ በራሱ ትልቅ አቅም ይፈጥራል ብለዋል።

የአዊ ድንች ብራንድ ሆኖ የገበያ ትስስር የተፈጠረለት በመሆኑ አሁን አርሶ አደሮች እያመረቱ ካለው በእጥፍ ማምረት ይችላሉ። ለዚህም የግብዓት አጠቃቀም፣ የማሳና የዘር አይነቶች ወሳኝ ናቸው። ስለዚህ እንደቦታና ግብዓት አጠቃቀም የሚገኘው ምርትም ይለያያል። ለአብነትም በአሁኑ ወቅት በአንድ ሄክታር ከ60 እስከ 80 ኩንታል ድንች የሚመረት ሲሆን፣ በቀጣይ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በሄክታር እስከ 120 ኩንታል ማምረት ይቻላል።

በአዊ ዞን አካባቢ የሚመረተው ድንች ለጤና እጅግ ተስማሚ፣ ጣፋጭ እንደሆነና ሶስት አይነት ዝርያ ያለው መሆኑን የጠቀሱት አርሶ አደር ምክሩ፣ እነሱም ቾልታ፣ አትርአበባና በለጠ ሲሆኑ፣ ሶስቱም የድንች አይነቶች ብራንድ ሆነው ተመዝግበዋል።

የድንች ዋጋ እንደ ገበያው ሁኔታ ከፍና ዝቅ ይላል። በአካባቢው ረከሰ ሲባል በኪሎ እስከ 10 ብር ሲወደድ ደግሞ እስከ 15 ብር ይሸጣል። በአካባቢው ድንችን ከምግብነት ባለፈ የድንች አረቄ ተሞክሮ ተወስዷል። ከስንዴ ዱቄት ጋር በመቀላቀልም እንጀራ መሆን እንደሚችል ተረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪም የአካባቢው ማህበረሰብ የራሱን ምርት በራሱ መጠቀም እንዲችል የድንች ችፕስ ፋብሪካ ለመትከል ዕቅድ ተይዟል።

የግብርና ሚኒስቴር የኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ የግብርና ምርቶች ወደ ገበያ የሚገቡት ደረጃ ወጥቶላቸው የሚታወቅ የምርት ብራንድ ይዘው እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ ይህም የገበያ ተወዳዳሪነትን እየተፈታተነው እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ይህን ችግር መነሻ በማድረግም የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የተለያዩ አይነቶች ድንች በሚመረትባቸው ክልሎች የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር፣ ምርታማነትን ማሳደግና የምርቶቹን የግብይት ስርዓት ማዘመን ትኩረት የሚሹ መስኮች መሆናቸውን በማመን ፕሮግራም ተቀርጾ ወደ ተግባር ተገብቷል።

ከእነዚህም መካከል የግብርና ምርቶች የራሳቸውን የጥራት መነሻ መሰረት ያደረገ መለያ ብራንድ በማውጣት ለገበያ ማቅረብ አንዱ ነው። በአሁኑ ወቅትም ሙዝ፣ አፕልና ድንች በብዛትና በጥራት በማምረት ያለውን ሰፊ የአገር ውስጥና የውጭ ገበያ እድል ለመጠቀምና የተዛባ የገበያ ስርዓቱን ለመለወጥ እየተሰራ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታዋ ጠቅሰው፣ ምርቶቹ በሚመረቱባቸው ክልሎች የራሳቸው ብራንድ እንዲኖራቸው ተደርገው ቀርበዋል። ይህም በግብይት ሥርዓቱ የሚስተዋሉ ችግሮችን በብዙ መልኩ መቅረፍ የሚያስችል እንደሆነም ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ጠንካራ የብራንድ እሴቶችን መለያዎች በመፍጠር ታላቅ እውቅና እንዲጎናጸፉ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እና በአማራ ክልሎች ከሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራት፣ የህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች፣ የግብርና ቢሮዎችና የዞን አስተዳደሮች ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በከፍተኛ ትጋት እየሰራ እንደሆነም ጠቅሰው፣ የግብርና ሚኒስቴርም ሥራውን በቅርበት እየተከታተለ መሆኑን ነው ያስረዱት።

እሳቸው እንዳሉት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለምርት እሸጋ፣ ለመሰረተ ልማት፣ ጥራት ባለው አገልግሎት አሰጣጥ፣ ለምርት ማጓጓዣ፣ ለፕሮሞሽንና ለማስታወቂያና ለመሳሰሉት ሥራዎች ትኩረት በመስጠት ይሰራል። በአሁኑ ወቅትም ብራንድ የተደረጉት የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንችና የጨንቻ አፕል አዳዲስ የብራንድ እሴቶችና መለያዎች ምርቶቹ ሰፊ የገበያ መዳረሻዎች እንዲኖራቸው በማድረግ የምርቶቹን ዋጋ ለማረጋጋትና የአርባ ምንጭ ሙዝ በተለየ በሂደት ዓለም አቀፍ ገበያ ጭምር እንዲያገኝ ያስችላል።

በመድረኩ ላይ እንደተጠቆመው፤ የአርባ ምንጭ በአገሪቱ በስፋት ዕውቅና ካላቸው የሙዝ ዝርያዎች ቀዳሚው ሲሆን፣ በኦርጋኒክነቱ በተለየ ጣዕምና ጥራቱ እንዲሁም ባለው ረጅም የቆይታ ጊዜ ይወደዳል። የጨንቻ አፕልም እንደዚሁ ባለው ልዩ ጣዕም፣ አነስተኛ የአሲድ መጠንና በውስጡ በያዘው የፈሳሽ ይዘቱ ጥቅጥቅ ያለ መሆኑና ሲበላ ለጥርስ ምቾት ያለው በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል። የአዊ ድንች ደግሞ የተጠቀጠቀ፣ ጥሩ ቅርጽና ልስላሴ ያለው ሲሆን፣ በተለያየ የምግብ አይነት ተቀቅሎ፣ ተጋግሮና ተጠብሶ ሊበላ የሚችል ኃይል ሰጪና ሌሎች የምግብ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ነው።

በሶስቱ የግብርና ምርቶች ማምረት ስራው ውስጥ በቀጣይ በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት አባል ያልሆኑ በርካታ አርሶ አደሮችም ገብተው ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል። በተመሳሳይ በሌሎች የአገሪቱ ክልሎች የሚገኙ የህብረት ሥራ ማህበራትም ስራቴጂክ ተብለው በተለዩ የግብርና ምርቶች ላይ የብራንድ እሴቶችና መለያዎች የመፍጠር ሥራ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህም መሰረት በሶማሌ፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ እና ኦሮሚያ ክልል በቅደም ተከተል የሚገኙት የፍየል፣ ማንጎና ቀይ ሽንኩርት ምርቶችን ብራንድ በማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ የግብርና ሚኒስቴር እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጧል።

በሶስቱ የግብርና ምርቶች ማለትም በሙዝ 140 ሺ 355 አባላት ያሏቸው 30 መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፤ በአፕል 242 ሺ 906 አባላትን ያቀፉ 12 መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም በድንች 69ሺ 984 አባላትን ያቀፉ 29 የህብረት ሥራ ማህበራት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

# የልጅ መካሪ

ዋለልኝ አየለ

ከተከራየሁበት ግቢ ውስጥ አንድ ሽምግል ያለ ሰውዬ አለ። ማታ ከሥራ ስገባ ወይም ሲገባ ከተገናኘን ትንሽ ቆም ብለን እናወራለን። በ‹‹ፀበል ቅመሱ›› እና በሌሎች የማህበራዊ ሕይወት አይነቶች ከተቀመጥን ደግሞ ረዘም ላሉ ሰዓታት እናወራለን።

በእነዚህ ሁሉ ጨዋታዎቻችን ውስጥ ስለልጁ ሳያወራልኝ አያልፍም። የሁልጊዜ ምክሩም ልጅ መውለድ እንዳለብኝ ነው። የአንድ ሰው መኖር ዋጋ የሚኖረው በልጅ ውስጥ እንደሆነ ያስረዳኛል። አለበለዚያ ተስፋ ቢስና ግድየለሽ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ ለግለሰቡ ብቻ ሳይሆን ለአገርም ጉዳት እንደሆነ ይነግረኛል።

ስለራሱ ሕይወትም ያጫውተኛል። ከባለቤቱ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ተፋተዋል። ዳሩ ግን ልጅ አለው። ልጁን እያስተማረ ዩኒቨርሲቲ የሚገባበት ጫፍ ላይ አድርሶታል። ልጅ የወለደውም በወጣትነቱ አይደለም። ያንን ልጅ ባይወልድ ኖሮ ጤናማ ሕይወት እንደማይኖረው ደጋግሞ ይነግረናል። በመኖሩ የሚደሰተው ልጁን ሲያይ ነው፤ የልጁን የነገ ደረጃ ሲያስብ ነው። ልጁም በዚያው ልክ የአባቱን ደስታ ያውቃል።

የዚህን ሰውዬ ሕይወት ያስታወሰኝ ባለፈው እሁድ የአንድ አባትና ልጅ ግንኙነት አስተውዬ ነው።

ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር በመንደር መሃል ባሉ የኮብልስቶን መንገዶች ውስጥ እየሄድን ነው። ወደ ዋናው መስመር ልንገባ ትንሽ ሲቀረን በመንደሮች መሃል ባለው መንገድ ላይ አንዲት ደሳሳ ቤት ውስጥና ውጭ ሰዎች ተሰባስበዋል። አረቄ ቤት ናት።

አንድ ወጣት ከቤቷ በር ላይ ራቅ ብሎ ከፊት ለፊቷ ያለ አጥር ሥር በከፍተኛ ድምጽ ይናገራል፤ አጠገቡ አንድ አባት አንገታቸውን ደፍተው ያዳምጡታል። ሌላው ሰው ግራና ቀኝ ሆኖ ግማሹ ያዳምጣል፤ ግማሹም ተመስጦ የራሱ ዓለም ውስጥ ነው። አረቄ ቤቷ በር ላይ የተመሰጡት ሰዎች ግን የልጁን ምክር እያዳመጡ ሳይሆን በራሳቸው ዓለም ውስጥ ናቸው።

ፍጥነታችንን ከመቀነስም አልፈን ቆም አልን። ወጣቱ ልጅ በኃይል እየተናገረ የነበረው አባቱን ነው። አባቱ መሆኑን ያወቅንም ጠይቀን ሳይሆን በሚናገራቸው ነገሮች ነው። ልጁ ቁጣ የቀላቀለ ምክር ያወርደዋል። በአባትየው ተደጋጋሚ አረቄ ቤት መሄድ የተሰላቸ ይመስላል። ‹‹ዝም ብልህ እኮ ትንሽ ቆይተህ ደግሞ ሴተኛ አዳሪ ቤት ነበር የምትገኘ!›› ብሎም መረር ያለች ቃል ተናገረ። ይሄ ሁሉ ሲሆን አሁንም አባትየው አንገታቸውን ደፍተው ፀጥ ብለው ያዳምጣሉ። አይቆጡም ወይም አጥፍቻለሁ ማረኝ አይሉም።

ከሁኔታው እንደተረዳነው አባትየው ከዚህ በፊትም ‹‹ተው›› ተብለው ያልተው ናቸው። ልጅየው እናቱ በዚህ ድርጊት እንደተሰላቹ ይናገራል። ወደ ምክሩ ሲመለስም ‹‹አንተ አረቄ ለአረቄ ቤት እየሄድክ እኔም ጠጪና አጫሽ ብሆን ‹ተው› ትለኝ ይሆን?›› እያለ አባቱን የምጸት ጥያቄ ይጠይቃል።

በዚሁ ሁኔታ ውስጥ ከአባትየው አንዲትም ቃል ሳንሰማ እጃቸውን ከኪሳቸው ከተው፤ አንገታቸውን ደፍተው ወደ ዋናው አስፋልት ከሚያስወጣው መንገድ በተቃራኒ ሄዱ(ወደ ቤታቸው መሰለን)። ልጁም ቁጣ ከቀላቀለ ንግግሩ ለዘብ ብሎ ምክር ብቻ እያወራ ተከተላቸው። እኛም ወደ መንገዳችን ሄድን።

ሁለቱንም ነው ያመሰገንኳቸው። እንዲያውም ከአባትየው ልጀምር። በነገራችን ላይ አባትየውን ሳመሰግን ከጓደኛዬ ጋር የተለያየ ሀሳብ ስለያዝን እየተከራከረን ነበር። እንዴት በዚህ ዕድሜያቸው፤ ለዚያውም ቤተሰብ እያላቸው ይጠጣሉ ነው የጓደኛዬ ወቀሳ። ይሄ ግልጽ ነው። ቤተሰብ እያላቸው ለዚያውም በስተርጅና ከአረቄ ቤት እየተፈለጉ መምጣት አልነበረባቸውም።

ከዚህ በተጓደኝ ግን አንድ ያመሰገንኩባቸው ነገር አለ። ሰውየው ልጃቸው ሲመጣ በጣም ነው ያፈሩት፤ በጣም ነው የተጸጸቱት። ያ ልጁ ሲናገረው የነበረው ሁሉ እውነት ነው ብለው ተቀብለዋል ማለት ነው። እርግጥ ነው ከድርጊታቸው ካልታቀቡ ፀባይን ማሳመር ብቻ የቤተሰቡን ጥያቄ አይመልስም። ግን ደግሞ ከሌላው ሰካራም ሁሉ ይለያሉ።

የሰካራም ትልቁ ችግሩ እኮ ገንዘብ ማጥፋቱ ወይም ጤናው መጎዳቱ ብቻ ሳይሆን ቤት ገብቶ መበጥበጡ ነው። ምንም እንኳን ሰውየው ቤት ሲገቡ ምን እንደሚሉ ባናውቅም ልጁ ሲቆጣቸው ካሳዩት ዝምታ ተነስተን ግን እዚያም ምንም እንደማይሉ መገመት ይቻላል።

ሰውየውን ማመስገን የፈለኩት የሚያስመሰግን ሥራ ሰርተው አይደለም፤ መጠጥ ቤት መገኘት ምኑም አያስመሰግንም(ለዚያውም በዚያ ዕድሜያቸው)። ከእርሳቸው የሚጠበቅ መካሪነትና አስተማሪነት፤ አርዓያነት ነው።

ያመሰገንኩባቸው ግን አንድ ነገር አለ፤ ይህንኑም አድርገው ከልጁ ጋር ‹‹ምን አገባህ!›› በሚል ወደ ስድድብ አለመግባታቸው። ልጃቸው ከመጠጥ ቤት ገብቶ ‹‹ውጣ!›› ሲላቸው ሹልክ ብለው መውጣታቸው ቢያንስ በከፊል አያስመሰግናቸውም?

ወደ ልጅየው ስንመጣ ትልቁ ምስጋና ለእርሱ ነው። አስቡት! ወጣት ነው። ወጣቶች በምን እንደሚታሙ የምናውቀው ነው። በመጠጥና በሌሎች አደንዛዥ ሱሶች የተጠመዱ ናቸው። ከእናትና አባት ተደብቀው መጠጥ ቤት ይሄዳሉ፤ ይህ የነገርኳችሁ ገጠመኝ ግን በተቃራኒው ነው። ልጅየው መጠጥ ቤት ተገኝቶ አባትየው ሊያስወጡት መጥተው ቢሆን ኖሮ ብየ አሰብኩ፤ ምናልባትም ‹‹አሻፈረኝ›› ማለቱ አይቀርም ነበር።

ልብ አላልንም ወይም አጋጣሚውን አላገኘን ይሆናል እንጂ እንዲህ አይነት የልጅ አዋቂ፣ የልጅ አሳቢ፣ የልጅ መካሪዎችም አሉ። እንዲያውም እኮ የተማረ መሃይም ሆነን እንጂ ከአዛውንት አባቶች የተሻለ ዕድሜያችንን በትምህርት ያሰለፍን ወጣቶች ነበር አይደል? አባቶች ወጣት በነበሩበት ዘመን አሁን ያለው ሰፊ የትምህርት ዕድል አልነበረም፤ እንዲህ በቴክኖሎጂ የረቀቀና የፈጠነ አልነበረም። ጊዜያቸውን በትምህርት ላይ ስለማያሳልፉ መጠጥ ቢለምዱ አይደንቅም። አስደናቂ የሚሆነው ግን የዚህ ዘመን ወጣት ይሄ ሁሉ አማራጭ እያለው ጊዜውን መጠጥ ቤት ሲያሳልፍ ነው።

በነገራችን ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ስለሆነ እንጂ ገጠር አካባቢ ብዙ ጊዜ ጠጪዎች አባቶች ናቸው። ልጅ አባቱን ‹‹ለምን ትጠጣለህ?›› እያለ ሲመክርና ሲቆጣ ነው የሚታየው። አዲስ አበባ ውስጥ ግን አባትና እናት ልጃቸውን ሲቆጡና ሲቆጣጠሩ ነው የሚታየው። ይህ የሆነው ደግሞ ሱስ ቦታ የሚገኙ ከአባቶች ይልቅ ልጆች ስለሆኑ ነው።

ወጣቶችም ሆኑ አባቶች እንዲህ ቢሰማሙና ቢመካከሩ ሁሉም ነገር ይሰምር ነበር።

ስለልጁ ደጋግሞ የሚነግረኝ ጎረቤቴ ትዝ ያለኝ በዚህ ገጠመኝ ነው። እኚህ ልጃቸው የተቆጣቸው ሰውዬ እንዲህ ጎብኚ ያገኙት ልጅ ቢኖራቸው አይደል? ተቆርቋሪ ቢኖራቸው አይደል? ሹልክ ብለው የሄዱት ልጃቸው ቢሆን አይደል?

እኚህ ሰውዬ ልጅ ባይኖራቸው ኖሮ እስከሚወድቁ ድረስ ይጠጡ ነበር፤ እንዲህ እንዲህ እያሉ ጎዳና ላይ ይወጡ ነበር። ልጅ ጧሪም መካሪም ይሆናል!

# ዓለም አቀፍ

## በኢራን ፋብሪካ ላይ እሳት ያስነሳ የበይነ መረብ ጥቃት ተፈጸመ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በዚህ ዘመን አገራትን ከሚያሳስቡ ጥቃቶች መካከል ቀዳሚው በበይነ መረብ በኩል የሚፈጸሙት እየሆኑ ነው። በበይነ መረብ በኩል የሚፈጸም ጥቃት የአገራትን የትራንስፖርት፣ የኃይል እና ሌሎች የመሠረታዊ አገልግሎቶችን በማቃወስ እያንዳንዱን ዜጋ ይነካል። እስካሁን ባለው ልምድ በበይነ መረብ በኩል የሚፈጸሙ ጥቃቶች መረጃዎችን በማዛባት እና በማስተጓጎል የተለመዱትን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎችን በማወክ፣ በአገራት ደኅንነትና ምጣኔ ሀብት ላይ ቀውስን ሲፈጥሩ ነው የሚታወቁት።

አሁን ግን በበይነ መረብ በኩል የሚፈጸሙት ጥቃቶች የሚታዩ ተጨባጭ፣ ቁሳዊና እና አካላዊ ጉዳትን ማድረስ እንደሚችሉ የሚያመለክቱ ክስተቶች እየታዩ ነው።ይህም መረጃዎችን በመመዝበር በሚታወቁት የበይነ መረብ ሰርሳሪዎች (ሃከርስ) አማካይነት የሚፈጸም ጥቃት ነው።

እንዲህ አይነቱ ተጨባጭ ጉዳት የሚያደርስ ጥቃት ከሁለት ሳምንት በፊት በኢራን የብረት ብረት ማምረቻ ፋብሪካ ላይ ተፈጽሞ፣ በበይነ መረብ በኩል የሚታይ እና የሚዳሰስ ጥቃት ሊፈጸም እንደሚችል ማሳያ ሆኗል። ለዚህ ጥቃት ‘ፕሬዳቶሪ ስፓሮው’ የሚባል የበይነ መረብ ሰርሳሪ ቡድን ኃላፊነቱን ወስዷል። ቡድኑ በኢራኑ ፋብሪካ ላይ ከባድ የእሳት ቃጠሎን እንዳስነሳ በመግለጽ፣ ይህንንም የሚያሳይ የቪዲዮ ማስረጃ ይፋ አድርጓል።



ቪዲዮው በደኅንነት ካሜራ የተቀረጸ ሲሆን፣ አንደኛው ማሽን በእሳት ተያይዞ የቀለጠ ብረት መርጨት ከመጀመሩ በፊት የብረት ማቅለጫ ፋብሪካው ሠራተኞች ከቦታው ሲወጡ እና በመጨረሻም እሳቱን ለማጥፋት ሲጥሩ ይታያሉ። በሌላ ቪዲዮ ላይ ደግሞ አንድ የፋብሪካው ሠራተኞች የእሳት አደጋ ሠራተኞች እንዲጠሩና በማሽን ላይ ስለደረሰው ጉዳት ጮክ ብሎ ሲናገር ይታያል።

ከዚህ ጥቃት ጀርባ እንዳለ የሚናገረው ‘ፕሬዳቶሪ ስፓሮው’ ባለፈው ሰኔ ወር ማብቂያ ላይ በኢራን የብረታ ብረት ማምረቻዎች ላይ ሦስት ጥቃቶችን መድረሱን አመልክቷል። ለዚህም በግልጽ ያላብራራውና በኢራን ተፈጽመዋል ላላቸው “የፀብ አጫሪነት” ድርጊት ምላሽ ነው ብሏል። ከዚህ በተጨማሪም ቡድኑ ከፋብሪካዎቹ ሰረቅኳቸው ያላቸውን ምስጢራዊ ኢሜይሎችን ጨምሮ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን መረጃዎች ይፋ ማድረግ ጀምሯል።

የበይነ መረብ ሰርሳሪው ‘ፕሬዳቶሪ ስፓሮው’ በቴሌግራም ገጹ ላይ እንዳሰፈረው የጥቃቱ ኢላማ የሆነት ፋብሪካዎች “ዓለም አቀፍ ማዕቀብ የተጣለባቸው ቢሆንም ሥራቸውን ቀጥለዋል። በተፈጸሙት የበይነ መረብ ጥቃቶቻችን ንጹሃን ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ አድርገናል።” ይህም የበይነ መረብ ሰርሳሪዎች የሚፈጽሙት ጥቃት የሰዎችን ሕይወት አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል መግለጻቸው፣ እንዲህ አይነቶቹ ጥቃቶች አካላዊ ጉዳት ማድረስ ወደሚችሉበት ደረጃ መሸጋገራቸውን ያመለክታል። ይህም አገራትን ከሚያሳስባቸው ጉዳይ አንዱ መሆኑ ተነግሯል።

ጥቃት ፈጻሚዎቹ በሰው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ያደረጉት ጥንቃቄ ሙያተኞች መሆናቸውንና በመንግሥት የሚደገፉ ወታደራዊ የበይነ መረብ ሰርሳሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ጥርጣሬንም ፈጥሯል። ጥቃቱን ከመፈጸማቸው በፊትም ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በመገምገም በጥንቃቄ መደረጉ የመረጃ መረብ ጥቃት ወደ ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን አመልካች ነው።

ከእስራኤልና ከአሜሪካ ጋር ፍጥጫ ውስጥ ያለችው ኢራን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከታታይ የበይነ መረብ ጥቃቶች ኢላማ ሆናለች። ከዚህ በፊት የተፈጸሙት ጥቃቶች የራሳቸው የሆነ ተጽእኖን ያስከተሉ ቢሆንም የአሁኑን አይነት ግን ከባድ ተጨባጭ ጉዳትን አላደረሱባትም። ከ12 ዓመት በፊት ኢራንን ከምዕራባውያን ጥርስ ውስጥ ባስገባት የዩራኒየም ማበልጸጊያ ማዕከሏ ላይ ‘ስተክስኔት’ የተባለው የበይነ መረብ ጥቃትም እንዲሁ በተቋሙ ላይ ተጨባጭ ጉዳትን አስከትሎ ነበር።

ይህ ‘ስተክስኔት’ የኮምፒውተር ቫይረስ ጥቃት፣ ናትዛን በሚባለው ቦታ ኢራን ባላት የዩራኒየም ማበልጸጊያ ማዕከል ውስጥ ያሉ ማብላያዎችን በመጉዳት ወይም ማውደም፣ የአገሪቱን የኑክሌር ፕሮግራምን አደናቅፎታል ተብሎ ይታመናል። ከዚያ በኋላ ግን እንዲህ አይነቱ ተጨባጭ ቁሳዊ ጉዳትን ያደረሱ የተረጋገጡ በጣም ጥቂት ጥቃቶች ብቻ አጋጥመዋል።

ተመሳሳይ ጥቃት ጀርመን ውስጥ በ2014 (እአአ) ተከስቶ በአንድ የብረት ፋብሪካ ላይ “ከባድ ጉዳት” በማድረስ ሥራው እንዲቆም ማስገደዱን የአገሪቱ የመረጃ መረብ ደኅንነት ባለሥልጣን ያወጣው ሪፖርት አመልክቷል። በተጨማሪም የመረጃ መረብ ሰርሳሪዎች የአንድ የውሃ ማጣሪያ ተቋም የመረጃ መረብን ሰብረው በመግባት በውሃ አቅርቦቱ ላይ ኬሚካል ለመጨመር ሞክረው ከሽፎባቸዋል። ይህ ጥቃት ቢሳካ ኖሮ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ ይችል ነበር ተብሏል።

በይነ መረብ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የትራንስፖርት ሥርዓትን በማወክ መስተጓጎል ከመፍጠር ባሻገር ተጨባጭ ጉዳትን ሲያስከትሉ አልታዩም ነበር። ይህ በኢራን ላይ ተጨባጭ ጉዳትን ያስከተለው የ‘ፕሬዳቶሪ ስፓሮው’ የበይነ መረብ ጥቃት ወዴት ሊያመራ እንደሚችል እስካሁን አልታወቀም። ይህ ጥቃት በአንድ አገር አማካይነት የተፈጸመ ከሆነ ግን ኢራን ዓለም አቀፍ ሕግን መሠረት አድርጋ ምላሽ ለመስጠት ያስችላታል ሲሉ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያስጠነቅቁ ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## የአከርካሪ አጥንት ህክምና እናት

አስናቀ ፀጋዬ

«ካይሮፕራክቲክ» የአጥንት፣ የነርቭ ፣ ጡንቻና በተለይ ደግሞ የአከርካሪ አጥንት ላይ የሚያተኩር የህክምና ዘርፍ መሆኑን በዚህ ዘርፍ ያሉ የህክምና ባለሞያዎች ያስረዳሉ። ይህ የህክምና ዘርፍ ግን በኢትዮጵያ ብዙም የተለመደ ባለመሆኑ ትምህርቱ በኮሌጅ አልያም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሲሰጥ አይታይም። በአፍሪካም ቢሆን ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር በሌሎች አገራት ትምህርቱ አይሰጥም።

ከዚህ በመነሳት ታዲያ አንድ የአገር ባለውለታ በአገራቸው ያዩትን የአከርካሪ አጥንት ጤና ችግር በዝምታ ለማለፍ አልፈቀዱም። ይልቁንም በአሜሪካን አገር ለአስራ ሁለት አመታት ሲሰሩበት የቆዩትን የአከርካሪ አጥንት ህክምና ሞያ ይዘው ከሃያ አንድ አመት በፊት ወደ አገራቸው በመመለስ የመጀመሪያውን የአከርካሪ አጥንት ህክምና ማእከል አቋቁመዋል።

እኚህ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሆኑት የአከርካሪ አጥንት ሀኪም የተለያዩ በጎና አነቃቂ ንግግሮችን በማድረግም ይታወቃሉ። በህክምና ሳይንስ ውስጥ በተቻለ መጠን አብዛኛው ህክምና የአከርካሪ አጥንትን በማስተካከል ቢጀመር የተሻለ ነው የሚል እሳቤም አላቸው። በኢትዮጵያ የአከርካሪ አጥንት ህክምና ማዕከል ለማቋቋም የተነሱበት አላማም ይኸው ነው።

በተለይ ደግሞ «አስር ለጤና» በሚለው መርሀግብራቸው ሰዎች ከባድ ስራ ከመስራታቸው በፊት ሰውነታቸውን እንዲያሟሙቁ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉና ከውስጣቸው እንዲተነፍሱ በማድረግ ውጤታማና ጤነኛ ሰራተኛ እንዲፈጠር ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

በትምህርት ቤቶችም «ቀጥ በልጅነት» የሚለውን መርሃግብር ተግባራዊ በማድረግ ልጆች የአከርካሪ አጥንታቸው ተስተካክሎ እንዲያድግ በሰውነት ማጎልመሻ መምህራን በኩል በርካታ ስራዎችን ያከናውናሉ። ሰዎች ስራ ከመጀመራቸው በፊት ለአስር ደቂቃ ያህል ከስራ ሰአታቸው ላይ ወስደው እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መንግስት በይፋ እንዲፈቅድ ግፊት እያደረጉም ነው- በአከርካሪ አጥንት ህክምና ሞያ ከሰላሳ አመት በላይ የቆዩት የፈርስት ስፓይን ሴንተር መስራችና ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ሰላም አክሊሉ።

ዶክተር ሰላም አክሊሉ እድገትና ውልደታቸው በድሬዳዋ ከተማ ነው። ለቤተሰባቸው ስምንተኛና የመጨረሻ ልጅ ናቸው። በእናትና አባታቸው፣ በታላላቅ እህትና ወንድሞቻቸው ፍቅርና እንክብካቤ አግኝተው ነው ያደጉት። ለእድገታቸውና ለዛሬ ማንነታቸው የበርካታ ሰዎች አስተዋፅኦ ያለበት ቢሆንም የአባታቸው ድጋፍ ግን የተለየ ነው። አባታቸው በተለይ ለሴት ልጆች ያላቸው አስተሳሰብም ከፍተኛ የነበረ በመሆኑ በማንነታቸው ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ዶክተር ሰላም ገና የአስራ ሰባት ዓመት ታዳጊ እያሉ ወደ አሜሪካን አገር የመሄድ እድል ቢገጥማቸውም እርሳቸው ወደአሜሪካን አገር የሄዱበት ግዜ ግን ጥሩ አልነበርም። ወቅቱም በኢትዮጵያ ቀይ ሽብር በከፍተኛ ሁኔታ የተፋፋመበት ነበር። «ከነገ ዛሬ እሞት ይሆን» ብለው የሚሰጉበትም ግዜም ነበር።

በግዜው በርካቶች በእርሳቸው እድሜ ያሉ ወጣቶችም በስጋት የሚኖሩበት ከባድ ውቅት የነበረ ቢሆንም አሜሪካን አገር ከሄዱ በኋላ ቀድመው የሄዱ እህቶቻቸውና ወንድማቸው ስለነበሩ እዛ ብዙ አልተቸገሩም። አሜሪካን አገር ከገቡ በኋላም ከመጡበት የአገራችው ልምድ ተነስተው በፍፁም እንደ እድሜያቸው መሆን እንደማይችሉ ያውቁ ነበር። የኋላ ኋላ ግን ራሳቸውን ማስተማርና ህይወታቸውን መለወጥ እንዳለባቸው ተረድተዋል።

ከዚህም በመነሳት ገና በአስረኛው ቀን ነበር አሜሪካ ስራ የጀመሩት። በአሜሪካ ትምህርት ለመማር አስቸጋሪ ስለነበርም ለስድስት አመታት ያህል በምሽት እየሰሩ ነበር ትምህርታቸውን የተከታተሉት።

ከልጅነታቸው ጀምሮ ሃኪም የመሆን ህልም



ዶክተር ሰላም አክሊሉ፤

የነበራቸው ዶክተር ሰላም አክሊሉ ይህ ምኞታቸው የጀመረው ገና የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሳሉ ነበር። የ9ኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ቁጭ ብለው ሲያጠኑ በሃያ ሰባት አመታቸው ዶክተር እንደሚሆኑ እቅድ ያወጡ ነበር። ዶክተር ሆነው ተመልሰው አብረዋቸው የተማሩ ተማሪዎችን እንደሚያናግሯቸውም ያስባሉ። :

በአሜሪካን አገር ቆይታቸው ዶክተር ሰላም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በኬሚካል ቴክኖሎጂ ኬሚስትሪ ሜጀር ከካሊፎርኒያ ትሬድ ቴክኒካል ኮሌጅ አግኝተዋል። በካይሮፕራክቲክ ህክምና የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከክሊቭላንድ ካይሮፕራክቲክ ሴንተር ተቀብለዋል። ገና ልጅ እያሉ ሀኪም የመሆን ምኞታቸውንም ያውም በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የአከርካሪ አጥንት ሃኪም በመሆን የኋላ ኋላ ማሳካት ችለዋል። በመቀጠል ደግሞ በዶክተር አፍ ሜዲስን ከሶቼካልኮ ሜክሲኮ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል።

በተማሩበት የካይሮፕራክቲክ ህክምና ሞያ የመጀመሪያዎቹን አስራ ሁለት አመታት በዛው አሜሪካን አገር ካሊፎርኒያ በሚገኝ አንድ የህክምና ማእከል ውስጥ ሰርተውበታል። ወደዚህ ሞያ የገቡትም በታላቅ እህታቸው አነሳሽነት ነበር። በተለይ ደግሞ በአፄ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ወደ አሜሪካን አገር ሄደው የካይሮፕራክተር ህክምና ትምህርት ከተከታተሉት የመጀመሪያዎቹ ሀኪሞች ውስጥ አንዱ ከነበሩት ከዶክተር ተስፋ ወሰኔ ጋር መገናኘታቸውና ማውራታቸው ወደዚህ ሙያ ለመግባት ይበልጥ ገፋፍቷቸዋል።

ከባለቤታቸው ጋር የተገናኙትም በዛው አሜሪካን አገር ሲሆን ከትዳር አጋራቸው ሁለት ወንድና ሁለት ሴት ልጆችን አፍርተዋል። በባለቤታቸው ሀሳብ ጠንሳሽነት ልጆቻውን ወደ አገራቸው ተመልሰው በኢትዮጵያዊ ባህል ማሳደግ ስለፈለጉ ከዛሬ ሃያ አንድ አመት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። ነገር ግን ወቅቱ ሰው ወደ አገሩ የሚመለስበት ምቹ ግዜ አልነበረም። ሆኖም ወደአገራቸው መመለሳቸውን በህይወታቸው ከወሰኗቸው ትክክለኛ ውሳኔዎች ውስጥ እንደዋና ይቆጥሩታል።

ከዛሬ ሀያ አንድ አመት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የመጀመሪያዋ ካይሮፕራክቲክ ሀኪም የነበሩት ዶክተር ሰላም፤ በኢትዮጵያ የካይሮፕራክቲክ ህክምና ማእከል በማቋቋምም ቀዳሚ ናቸው። ፈርስት ስፓይን ሴንተር የተሰኘና በአከርካሪ አጥንት ህክምና ላይ የሚሰራ ማእከልም አቋቁመዋል።

ማእከሉ በአዲስ አበባ ሶስት ክሊኒኮች ያሉት ሲሆን ከአዲስ አበባ ውጪ በድሬዳዋና ጅማ ከተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል። ዘጠና ሰባት የጤና ባለሞያዎችንም በውስጡ አቅፏል። በዋናነትም በአከርካሪ አጥንት ችግር ላይ አተኩሮ ይሰራል። በተጨማሪም የአንገት፣ ወገብ፣ ጀርባ፣ ትከሻ፣ እጅ፣ ዳሌ፣ ጉልበት፣እግር፣መገጣጠሚያ፣ ጡንቻና የነርቭ ህመም ህክምና አገልግሎቶችን ይሰጣል።

ማዕከሉ በኢትዮጵያ በአብዛኛው በቀዶ ህክምና ሲስተካከል የሚታወቀውን የዲስክ መንሸራተት ከቀዶ ህክምና ጋር በተያያዘ በርካታ አደጋዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ችግሩን ያለቀዶ ህክምና በተፈጥሯዊ መንገድ ለማስተካከል የፊዚዮቴራፒና የካይሮፕራክቲክ ሞያን ቀላቅሎ የተዛባውን የአከርካሪ አጥንት የማስተካከል ስራ ይሰራል። ይህም ዲስኩ ላይ ያለውን ጫና በማንሳት ነርቩ ላይ ያለውን እክል ማስተካከልን ያካትታል።

ማእከሉ ብዙ ሰዎች የቀዶ ህክምና እንዳያደርጉ በማስቆም የሚታወቅ ሲሆን በተቻለ መጠን ሰዎች ወደ ቀዶ ህክምና እንዳይሄዱ የመከላከልና የበለጠ ደግሞ ቀጣይነት ያለው የአከርካሪ አጥንት ማስተካከል ስራዎችን በማከናወን የተሻለና ጤናማ ህይወት እንዲኖራቸው ጥረት ያደርጋል።

በአሁኑ ግዜ ማእከሉ የመጀመሪያውን ከህመም ማገገሚያ ሆስፒታል እየገነባ ይገኛል። ከዚሁ ፕሮጀክት ጎን ለጎንም በውጭ አገራት ስራ ሰርተው አቁመው ወደአገራቸው የሚመለሱ ሰዎች በአንድ ላይ የሚሰባሰቡበት ማእከል እያዘጋጀ ነው። ማእከሉ 150 ሰዎች አብረው ሊኖሩበት የሚችል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ከውጭ አገር የሚመለሱ ዲያስፖራዎች ናቸው።

«የመላው ሰውነት ጤንነት መሰረቱ የአከርካሪ አጥንት አቀማመጥ ትክክል መሆን ነው» የሚሉት ዶክተር ሰላም ይህ ካልሆነ የሰዎች መላው ሰውነታቸው ጤነኛ ሊሆን እንደማይችል ይገልፃሉ። ከዚህ አንፃር በተለይ በግንባታና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ ከባድ ስራዎችን የሚሰሩ ሠዎች ችግሩን እንዲገነዘቡት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ። የአከርካሪ አጥንት ጤንነት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ባለሞያውም ጭምር ስለማያውቀው ስለጉዳዩ የማስገነዘብ ስራ እንደሚያስፈልግም ይጠቅሳሉ።

በዚህ መነሻነት ፈርስት ስፓይን ሴንተር «አስር ለጤና የሚል» አገራዊ ንቅናቄ እንዳስጀመረ ገልፀው፤ ይህም ሰዎች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ለአስር ደቂቃ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከልባቸውና ከትንፋሻቸው ጋር እንዲሆኑ ብሎም ሠውነታቸውን ለስራ እንዲያዘጋጁ የሚያስችላቸው መሆኑን ያብራራሉ።

ይህ አገራዊ ንቅናቄ ሰዎች የተረጋጋ ማንነትና ለስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ከማድረጉም በዘለለ አሰሪዎችም ምርታማ የሰው ሃይል እንዲኖራቸውና በዚህም ትርፋማ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው እንደሆነም ዶክተር ሰላም ይጠቁማሉ። ይህ ደግሞ ተደምሮ ሲታይ ጤናማ ህዝብ እንዲኖርና ለአገር ብልፅግናም ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው ያስረዳሉ።

«አስር ለጤና» የተሰኘው ፕሮግራም በሁሉም የግንባታና የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን በጤና ሚኒስቴር በኩል እንደፀደቀና በተመሳሳይ በሰራተኛና ማህራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩልም አውቅና እንዳገኘም ይገልፃሉ። ፕሮግራሙ በሁሉም የግልም ሆነ የመንግስት ተቋማት ቢተገበር ጤናማና የተሻለ ብሎም ምርታማ የሰው ሃይል እንዲኖር የሚያስችል መሆኑንም ይጠቁማሉ።

የፈርስት ካይሮፕራክቲክ ሴንተር ዋነኛ አላማም ይህንኑ «አስር ለጤና» የተሰኘውን ፕሮግራም በሁሉም ተቋማት ውስጥ በስፋት ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግና በቀጣዮቹ አምስት አመታት ይህንኑ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚያደርጉ አስር ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን መፍጠር መሆኑንም ዶክተር ሰላም ያብራራሉ።

«ይህ ፕሮግራም ከተጀመረ ወዲህ ውጤት እያመጣም ነው» የሚሉት ዶክተር ሰላም፤ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ሰራተኞቻቸው ላይ የጀመሩት ስራ ለዚህ ጥሩ ማሳያ መሆኑን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ። አንድ መስሪያ ቤት ወይም ተቋም ቢያንስ ለአንድ አመት ይህን ፕሮግራም ልምድ አድርጎ ሰርቶበት ለስራ ዝግጁ የሆነ የሰው ሃይል ይዞ መስራት ከቻለ የፕሮግራሙ ውጤታማነት እንደሚረጋገጥም ያስረዳሉ። ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ ትምህርት ቤቶችም ጭምር ተማሪዎቻቸው ፕሮግራሙን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማድረግ የማእከሉ ሌላኛው አላማ መሆኑንም ይጠቁማሉ።

በቀጣይም ማእከሉ እያንዳንዱ ሰው ሰውነት ራሱን የማዳን ሃይል እንዳለው ተገንዝቦ የራሱን ጤና እንዲጠብቅ የማብቃት ስራዎች በስልጠናና በልዩ ልዩ መንገዶች ለመስጠት እቅድ እንዳለው ይገልፃሉ። የአኗኗር ዘይቤዎችን ማስተካከል ላይ ማእከሉ በቀጣይ አተኩሮ ከሚሰራባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆኑንም ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ኃላፊነት ወስደው የራሳቸውን ጤና እንዲጠብቁ የሚያበቁ የጤና ባለሞያዎችን የማሰልጠን ስራም ማእከሉ በቀጣይ እንደሚያከናውን ይገልፃሉ።


በተለይ ደግሞ ማዕከሉ ሰዎች ስራ ከመጀመራቸው በፊት ከስራ ሰአታቸው ላይ አስር ደቂቃ ተወስዶ «አስር ለጤና» የሚለውን ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲያደርጉ በመንግስት በይፋ እንዲፈቀድ ሰፊ ጥረቶችን እንደሚያደርግም ዶክተር ሰላም ይናገራሉ።

እምብዛም ባልተለመደው አከርካሪ አጥንት ህክምና ሞያ ለሰላሳ ሶስት አመታት ያህል የቆዩት ዶክተር ሰላም ከሃያ አንድ አመታት በላይ በዚሁ ሞያ አገራቸውን በማገልገላቸው ይህን እንደ አንድ ስኬት ይቆጥሩታል። ወደአገራቸው ሞያውን ይዘው እንደመጡ ከጤና ሚንስቴር ጀምሮ ህብረተሰቡ ለሞያው የነበረው ግንዛቤ አነስተኛ እንደነበር ነገር ግን ዛሬ ላይ ይሄ ተለውጦ የካርይሮፕራክቲክ ህክምና ለጤና ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ህብረተሰቡ እየተረዳው መምጣቱም ለኔ ተጨማሪ ስኬት ነው ይላሉ። ሆኖም አሁንም በርካቶች በዚህ የአከርካሪ አጥንት ችግር ተጠቂ ከመሆናቸው በፊት መከላከል ላይ ያተኮሩ ስራዎችን በመስራት በሞያቸው ከዚህም በላይ ስኬታማ መሆን እንደሚፈልጉ ይናገራሉ።

የአከርካሪ አጥንት ጤናን መጠበቅ መሰረታዊ፣ ብዙ ወጪ የማያስወጣና ብዙ መድሃኒት የማያስገዛ የጤና አጠባበቅ ዘይቤ ስለሆነ በተለይ ለአፍሪካ ብቸኛው መልስ ይሆናል ብለው እንደሚያስቡና ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም እንዲሆን ለማድረግ እንደሚሰሩም ያማላክታሉ።

የአገር መሰረቱ ሰው ነውና የአከርካሪ አጥንት ጤንነት ጉዳይ ከሚንስቴር መስሪያ ቤቶች ጀምሮ የሁሉም ሰው ጉዳይ ሊሆን እንደሚገባም ገልፀው፤ በተለይ ደግሞ የአከርካሪ አጥንት ችግርን አስቀድሞ መከላከል ላይ በስፋት ሊሰራ እንደሚገባ ያሳስባሉ። በመንግስት በኩል ያሉ ጅምር ስራዎች ቢኖሩም በቀጣይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባቸውም ይጠቁማሉ።

# ስፖርት





## ቡናማዎቹ አዲሱን አሰልጣኝ ዛሬ ይፋ ያደርጋሉ

ቦጋለ አበበ

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ስመጥር የሆነው ሕዝባዊ ክለብ ኢትዮጵያ ቡና እንደ ገናና ስሙ የሊጉን ዋንጫ ደጋግሞ በማንሳት ስኬታማ መሆን አልቻለም። በርካታ አሰልጣኞችን ቢቀያይርም ውብ እግር ኳስን እንጂ የሊጉን ዋንጫ ለውብ ደጋፊዎቹ ከአንድ ጊዜ የበለጠ ማበርከት አልቻለም። ከሶስት ዓመት በፊት የክለቡን ባህልና አጨዋወት ጠንቅቆ የሚያውቀው የቀድሞ ተጫዋቹ ካሳዬ አራጌ ከሚኖርበት አሜሪካን አገር መጥቶ በዋና አሰልጣኝነት ክለቡን መምራት ሲጀምር ትልቅ ተስፋ ተጥሎበት ነበር። ይሁን እንጂ አሰልጣኝ ካሳዬ አራጌ ከክለቡ ጋር ከሶስት ዓመታት የበለጠ አብሮ እንደማይዘልቅ ተረጋግጧል።

አሰልጣኝ ካሳዬ አራጌ ወደ ኢትዮጵያ ቡና ከመጣ በኋላ ባለፉት 3 ዓመታት በቆየበት ጊዜ አምና በሊጉ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ጨርሷል። ኮከብ ተጫዋችና ኮከብ ግል አግቢ የነበረው አቡበከር ናስርን አስመርጧል። በየጨዋታው ያገኛቸውን ተጋጣሚዎቹን ሁሉ እግር ኳሳዊ በሆኑ ቁጥሮች በልጦ ማሳየት ቢችልም ደጋፊው የተራበውን ዋንጫ ግን ማሳካት አልቻለም። ለረጅም ጊዜ ተይዞ የነበረው የሊጉ የግብ ክብረወሰንም በእሱ ዘመንና ተጫዋች መሰበሩ ከሚጠቀሱለት ስኬቶች ቀዳሚ ናቸው። ሆኖም ለክለቡ ኃላፊዎች ይሄ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ ሊያሰናብቱት ወስነዋል።

በርካታ የአገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ሰሞኑን እንደዘገቡትም ኢትዮጵያ ቡና ከአሰልጣኝ ካሳዬ አራጌ ጋር ያለውን ውል ሐምሌ 30/2014 እንደሚያቋርጥ አሰልጣኙም በኃላፊነቱ የተረከባቸውን ንብረቶች እንዲመልስና የሐምሌ ወር ደመወዙም እንደሚከፈለው በመግለጽ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ደብዳቤ ካስገባ ቀናቶች አልፈውታል።



**አሰልጣኝ ተመስገን ዳና የኢትዮጵያ ቡና አሰልጣኝ እንደሚሆን በስፋት እየተነገረ ነው፣**

ኢትዮጵያ ቡና የወልቂጤ ከተማ አሰልጣኝ የነበረውን አሰልጣኝ ተመስገን ዳናን አዲሱ የክለቡ አሰልጣኝ አድርጎ መቅጠሩን ዛሬ ይፋ ያደርጋል ተብሎ እንደሚጠበቅም መረጃዎች ወጥተዋል። ኢትዮጵያ ቡናን የተቀላቀሉትና የሚቀላቀሉት ተጫዋቾችም በአሰልጣኝ ተመስገን ዳና ምርጫ መሆኑ ተጠቁሟል። የአሰልጣኝ ካሳዬ ተተኪ የሚሆነው አሰልጣኝ ተመስገን ዳና የመሆኑ መረጃ ከወጣ በኋላ የክለቡ ደጋፊዎች ተቃውሟቸውን እያሰሙ ሲሆን ለክለቡ የፈረሙትና ይፈርማሉ የተባሉ ተጫዋቾች ክለቡን ያጠናክራሉ ብለው እንደሚያምኑ ነገር ግን አሰልጣኙ ላይ እምነት እንደሌላቸው በመግለጽ ጠንካራ የሆነ ቅሬታቸውን እያሰሙ ይገኛሉ።

የአሰልጣኝ ተመስገን ዳና የኢትዮጵያ ከ20 አመት በታች ብሄራዊ ቡድንን በዋና አሰልጣኝነት እንዲመራ ከተመረጠበት 2010 ጀምሮ በፕሪሚየር ሊጉ ክለቦች ተፈላጊ መሆን ችሏል። አሰልጣኝ ተመስገን በ2011 የአሰልጣኝ አዲሴ ካሳ ምክትል ሆኖ ሀዋሳ ከተማን አሰልጥኗል። በ2012 የደቡብ ፖሊስ ዋና አሰልጣኝ ቢሆንም በኮቪድ ምክንያት ውድድሩ እስኪቋረጥ ሰርቶ 2013 ላይ እንደገና ከ20 አመት በታች ብሔራዊ ቡድኑን ተረክቦ አንድ አመት ተኩል አሰልጥኗል። አሰልጣኙ በሴካፋ ከ20 አመት ቻምፒዮና ሁለተኛ የወጣበት ታሪኩ ትልቁ ሆኖ ተመዝግቦለታል። ከብሔራዊ ቡድኑ መልስ ወልቂጤ ከተማ የክለቡ አሰልጣኝ ጳውሎስ ጌታቸው ጋር በተፈጠረ አለመግባባት 12 ጨዋታ ከመራ በኋላ በመለያየታቸው አሰልጣኝ ተመስገን ዳናን በመቅጠር የ2014 18 ጨዋታን እንዲመራላቸው በማድረግ የዘንድሮውን የውድድር አመት አጠናቋል።

አሰልጣኙ ለተመልካች በሚሰበው ምርጥ አጨዋወት የሚታወቅ መሆኑ ትኩረት የሚስብ ሲሆን የቡናን ማራኪ አጨዋወት ያስቀጥላል ተብሎ በአመራሮቹ ታምኖበታል። ከአሰልጣኝ ተመስገን ዳና ጋር ህጋዊ ውል ያላሰሩት የቡናማዎቹ አመራሮች ግን የደጋፊዎቹን ጫና ፈርተው ሀሳባቸውን ይቀይራሉ ? ወይስ ? በጀመሩት አዲሱ ፕሮጀክት ይቀጥላሉ የሚለው ጉዳይ ዛሬ ምላሽ የሚያገኝ ይሆናል።

የወልቂጤ ከተማን በ2014 የውድድር ዓመት ከሁለተኛው አጋማሽ በኋላ የተረከቡት አሰልጣኝ ተመስገን ዳና አሁን አዲሱ የኢትዮጵያ ቡና አሰልጣኝ እንደሚሆኑ ግን ባለፉት ጥቂት ቀናት የወጡ መረጃዎች አመላክተዋል።

በዘንድሮ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ በ42 ነጥብና 8 የግብ ዕዳ 6ኛ ደረጃ ላይ ሆኖ ያጠናቀቀው ኢትዮጵያ ቡና ከያዛቸው ተጫዋቾች መካከል በእስካሁኑ አምበሉ አማኑኤል ዮሐንስ፣ ተከላካዩ አስራት ቱንጆ፣ ሁለቱ ግብ ጠባቂዎች በረከት አማረና እስራኤል መስፍን፣ ታዳጊዎቹ ገዛኸኝና ሱራፌል ጨምሮ ከ10 የማይበልጡ ተጨዋቾች ብቻ ሲቀሩ ቀሪዎቹ ውል ያላቸው በስምምነት ውላቸው ያለቀ ደግሞ ውላቸው ሳይታደስ ቡድኑን እንዲለቁ የሚደረግ መሆኑ ከክለቡ ተጫዋቾች የተገኘ መረጃ ጠቁሟል። ክለቡ ውል ያላቸውን ተጫዋቾች በስምምነት እንዲለያዩ መጠየቅ መጀመሩም ታውቋል።

እስካሁን ባለው መረጃ በዲሲፕሊን ደመወዙን ከተቀጣው ዊሊያም ሰለሞን፣ ከሶስት ወር የደመወዝ ቅጣት በኋላ የመጀመሪያ ደመወዙን የወሰደው ታፈሰ ሰለሞንና ሚኪያስ መኮንን ጨምሮ አብዛኞቹ ቡድኑን እንደሚለቁ እየተገለጸ ነው። ኢትዮጵያ ቡና ከአቡበከር ናስር ዝውውር የተገኘውን ገንዘብ ለዘንድሮ ዝውውር እንዲውል መወሰኑም እየተነገረ ነው።

የክለቡ ፕሬዘዳንት መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ "ዘንድሮ ከመቼውም ጊዜ ደካማ የሆነ ውጤት እንዳይመዘገብ የምትችሉትን ጣሩ በቀጣይ የውድድር አመት ግን ውጤታማ አሰልጣኝና ለዋንጫ የሚፋለም ስብስብ ይኖረናል" ማለታቸው የሚታወስ ሲሆን የመቶ አለቃ ፈቃደ ንግግር በቀጣዩ አመት ሊመጣ የሚችለውን አሰልጣኝ በይፋ ባያሳውቅም ከአሰልጣኝ ካሳዬ አራጌ ጋር ግን እንደማይቀጥሉ ያመላከተ ሆኗል።

እስከ ትናንት ድረስ ቡናማዎቹ መስፍን ታፈሰን ከሀዋሳ ከተማ፣ መሀመድ ኑርን ከጅማ አባጅፋር እንዲሁም አብዱልከሪም ወርቁን ከወልቂጤ ከተማ፣ ሃይለሚካኤል አደፍርስና ዱሬሳ ዱቢሳን ከሰበታ ከተማ ለማስፈረም መስማማታቸው በስፋት ተዘግቧል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንዳስታወቀው የክረምቱ የተጫዋቾች የዝውውር መስኮት ዓርብ ሐምሌ 1/2014 በይፋ ይከፈታል ተብሎ ይጠበቃል።


### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ናይል ኢንሹራንስ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ ቢሻው በላይ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር/220205 በ30/6/2013 ዓ/ም እና በኮ/መ/ቁ/252694 በ11/8/2014 ዓ.ም በ23/10/2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት 1ኛ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 8 በፍ/ባለመብት ግቢ ቆሞ የሚገኝ የሠ/ቁ/ኮድ3-55691 አ/አ የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 2,500,000 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር) የስም ማዛወሪያ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 6 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ 8፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡2ኛ በዚሁ ክ/ከተማ የሚገኝ የሠ/ቁ/ኮድ3-66277 አ/አ የሆነ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን ብር) የስም ማዛወሪያ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 6 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡የተጫራቾች ምዝገባ 9፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ካሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ኢትዮ ክሬዲት ሲስተምስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በፍ/ባለዕዳ አፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 269607 በ25/10/2013 ዓ.ም እና በመ/ቁ 265736 ሚያዚያ 12 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ሮሆቦት የመኪና ማቆሚያ ግቢ የሚገኝ ኮንክሪት ፓምፕ ተሽከርካሪ ማሽን ላይ ያለ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ብር 1,954,017.15 እና የቦሎ ዕዳ 446,000 ያለበት ሆኖ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 1,200,000 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ብር ) ሆኖ ተጠቃቃሽ መዝገቦች ያሉበት ሆኖ ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ5፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ካሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የምልክቱ ባለቤት ስም፡ **ArcelorMittal** አድራሻው 24-26 Boulevard d' Avranches, L-1160 Luxembourg, Grand-Duchy of Luxembourg
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/4416/2014
3. የጥበቃ ጊዜው፡ ከ28/01/2022 እስከ 28/01/2029
4. የንግድ ምልክት፡
5. ባለቤቱ የንግድ ምልቱን የሚጠቀምበት በ12/06/2000 ዓ.ም በVol-LXXII. No. 162 ባወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው፡፡
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-306 6/11/2014 (13/7/2022)**

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የምልክቱ ባለቤት ስም፡ **SKYWORTH GROUP CO., LTD** አድራሻው Unit A, 15/F, West, Skyworth Building, Shennan Ave, Nanshan District, Shenzhen, Guangdong 518207, China.
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/6176/2015
3. የጥበቃ ጊዜው፡ ከ11/05/2022 እስከ 11/05/2029
4. የንግድ ምልክት፡ Skyworth
5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ13/04/2008 ዓ.ም በVol-LXXV. No. 103 ባወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው፡፡
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-306 6/11/2014 (13/7/2022)**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት እነ ወ/ሮ መታሰቢያ በቀለ እና በፍ/ባለዕዳ ኢንስፔክተር ዳንኤል ኩማ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 133068 በ21/3/2014 ዓ.ም እና በመ/ቁ 129462 በ10/2/2014ዓ.ም፤27/10/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ አያት ሳይት የቤ.ቁ 12/21 የሆነ ካርታ ቁጥር በ/ሀ/ያ/12/378/01 የሆነ በሟች ስም የሚገኝ የቤቱ ስፋት 63.51 ካ/ሜትር የባንክ ዕዳ 42,850.88 ያለበት መሆኑ ታውቆ የሆነው የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 254,040 (ሁለት መቶ ሀምሳ አራት ሺህ አርባ ብር ) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ በ9፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጎብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ካሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡ በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጎድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**